## ጥናት አንድ ፩ኛ ሳሙ ፩፡፩-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የሕልቃና አባት ስሙ ናሲብ ይባላል፣ ይህ ሰው ኤፍሬማዊ ነው፣ ሕልቃና ሁለት ሚስቶች ነበሩት፣ ፍናና የተባለችው ሚስቱ ልጆች ሲኖሯት ሐና ግን ልጆች አልነበሯትም፤ ቤተሰቡ በየዓመቱ ለእግዚአብሄር የሚሰዋ ቤተሰብ ነው። በዚህን ጊዜ በመቅደሱ ያገለግሉ የነበሩት ሁለቱ የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሃስ ነበሩ። የነዚህን ሁለት ሰዎች ስም መጠቀሱ፤ ምንም ያህል የጌታ አገልጋዮች በርኩሰትና በድፍረት ሃጥያት መሞላታቸው፤ ሕልቃናና ቤተሰቡ መስዋዕታቸውን ለማቋረጥ ምክንያት ሊሆናቸው እንደማይበቃ ለማስተማር ይመስለኛል።
2. ሕልቃና ይወድ የነበረው ሐናን ሲሆን፤ ይህንንም ፍቅሩን ለመግለጽ ይጠቀምበት የነበረው መንገድ ለፍናና ከሚሰጠው ስጦታ ለሐና እጥፍ አድርጎ መስጠትን ነው። ይህ ሰው ምንም ያህል ሚስቱን ቢወድ ሊሰጣት ያልቻለው ነገር ልጅ ነው። እኔ ከዚህ ሁኔታ የምማረው፤ ምንም ያህል ሰዎች ቢወዱን ሊያደርጉልን የሚችሉት ነገር ውስን እንደሆነና፣ ለውስጣዊው ጥያቄአችን መልስ ያለው ከእግዚአብሄር ዘንድ ብቻ መሆኑን ነው።
3. ከቁ10 ላይ እንደምንመለከተው ጸሎቷ የነፍስ ምሬት ያለበት እንደሆን ሲነግረን፣ በተጨማሪም ደግሞ ስትጸልይ ከብዙ እንባና ከብዙ ለቅሶ ጋራ እንደነበረም እንመለከታለን። ሐና ከዚህ በፊት ልጅ ለመውለድ በእግዚአብሄር ፊት እንደጸለየች አልጠራጠርም፤ ሆኖም የዛሬውን ጸሎቷን በሌሎች ቀናት ከጸለየቻቸው ጸሎቶቿ ይለያል የምልበት ምክንያት፤ ቁ9 ላይ እንደምናየው ከእርሷ ጋራ የነበሩት ሰዎች ይሉኝታ ሳትፈራ፣ የካህኑንም የኤሊን ነቀፋ ሁሉ አልፋ፣ ከአፏ የሚወጣ ቃል ብቻ ሳይሆን ከውስጥ ነፍሷ የመነጨ ጸሎት መሆኑ ከሌሎቹ ይለያል ብዬ አምናለሁ።
4. ኤሊ ከሃና ጸሎት ሊመለከት የቻለው የውጭ ሰውነቷን፣ ይኸውም የአፏን ሁኔታ ብቻ ሲሆን ይህም በጠዋቱ ሰክረሻል ወደሚለው ወደተሳሳተ ድምዳሜ አድርሶታል። ሐና ግን ልታስረዳው የሞከረችው የልቤን ማየት አልቻልክም፣ እኔ ግን በአምላኬ ፊት እያደረግሁ ያለሁት የአፌን ሳይሆን የልቤን ነገር እየነገርኩት ነው፤ ማለትም በውጫዊው ነግር አይተህ አትፍረድብኝ የሚል መልዕክት ነው ያስተላለፈችለት።
5. ሐና ጸሎቷ የእምነት እንደነበረ የሚጠቁመን ክፍል በቁ18 ላይ የሰፈረው ክፍል "ከዚያ በኋላ በፊቷ ላይ ሃዘን አልታየም" የሚለው ሃሳብ ነው። ሳሙኤል ማለት ከእግዚአብሄር ለምኜዋለሁ ማለት ነው። በተለመነበትና በተወለደበት ጊዜያት መሃል ቢያንስ ቢያንስ የዘጠኝ ወራት ልዩነት መኖር አለበት።
6. ይህ ጉዞ ለፍናና ከሌላው ሁሉ ጉዞዎች ለየት የሚለው የምታበሳጨውና የምታስለቅሰው ሰው አለመኖሩ ልዩ ያደርገዋል። የወገኖቻቸውን ልብ በሃዘን ለሚወጉት ሰዎች ትምህርት ይሆናል ብዬ የማስበው፤ እግዚአብሄር ቀን ቆጥሮ የተናቁትን እንደሚጎበኝ ቅን እንደሚመጣ ሲሆን፣ ለተበደሉት ደግሞ በእግዚአብሄር በራሱ ሰዓት ጊዜውን ጠብቆ ጸሎትን እንደሚመልስና ስድብን ከእኛ እንደሚያርቅ ያስተምራል እላለሁ።
7. ሐና በዚያው ክፍል ስትናገር እንደምንሰማት ሳሙኤልን የተቀበለችው ከእግዚአብሄር እንደሆነና ልጁ የጸሎት መልስ እንደሆነ ስለምታውቅና እርግጠኛ ስለሆነች ነው።
8. ፍናና ሐናን ማስቀጣቷና ማበሳጨቷ እየከፋ እንደሚሄድ የምንመለከተው በየዓመቱ ሐና ለእግዚአብሄር መስዋዕትዋን ለማቅረብ ከቤተሰቧ ጋራ ወደ ሴሎ ለመሄድ ስትነሳ ነበረ።

# ጥናት ሁለት 1ኛ ሳሙ 2፡1-36 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሐናን በዚህ ክፈል እግዚአብሄርን ስታመሰግን የምናያት ሲሆን፤ ይህ ድርጊቷ ጸሎት ተብሎ መጠራቱ ደግሞ ምስጋናም የጸሎት አንዱ ክፍል እንደሆነ ነው። 1ኛ ጢሞ 2፡1ና ፊሊ 4፡6 ማንበብ ይረዳል። ሐናን በምዕ 1 ውስጥ ስናያት በመከራ ውስጥ የምታልፍና ስለዚህም በጸሎት በእግዚአብሄር ፊት የመጣች፤ በምዕ 2 ውስጥ ስንመለከታት ደግሞ ጸሎቷ ተመልሶላት በደስታ ተሞልታ እግዚአብሄርን ስታመሰግን ትታያለች፤ ስለዚህም ያዘነ እንዲጸልይ፣ ደስ ያለውም እንዲዘምር የተነገረውን በህይወቷ ስትፈጽመው እናያታለን።
2. ሐና ምንም እንኳን ሳሙኤልን በመውለዷ እንደ እናት ደስ ሊላት እንደሚችል ባንጠራጠርም እንኳን፤ በዚህ ክፍል ግን ለእርሷ ዋነኛ የደስታ ምንጭ ሆኖ የምናየው ስጦታው ሳጥሆን ሰጪው እግዚአብሄር እንደሆነ እንመለከታለን። ይህ ድርጊቷና አመለካከቷ ትክክለኝ መሆኑን የሚያረጋግጥልን ክፍል ፊሊ 4፡4 “ምንጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ” በማለት ደስታችን ከምንም ነገር ይልቅ በጌታ ሊሆን እንደሚገባ በመደጋገም ይመክረናል።
3. ቁ15ትንና ቁ16ትን ስናነብ እነዚህ ምናምንቴ ሰዎች የልባቸውን ክፋት የሚፈጽሙላቸው የራሳቸው የሆኑ አግልጋዮች እንደነበሯቸውና እነዚያን ሰዎች መጠቀሚያ እንዳደረጓቸው ይታያል። ከአገልጋዮቹ ብልሹ ምግባር የተነሳ ለእግዚአብሄር ማቅረብ ያለባቸውን መስዋዕት በደስታ ለማምጣት እንደተቸገሩ ነው የምናነበው። ከዚህ ክፍል ልንማር የምንችለው አገልጋይ ሲያጠፋ የራሱን ህይወት ብቻ የሚጎዳ ሳይሆን በሚያገለግለውም ህዝብ ህይወት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ያስተምረናል።
4. ሳሙኤል ገና ልጅ ስለነበረና የክህነት አገልግሎት ላይም እንዳልተሰማራ ማሰብ አያስቸግርም፤ እኔ እንደሚመስለኝ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ማናቸውም አይነት ስራ፤ ቤት ማጽዳት ቢሆን፣ መላላክ ቢሆን፣ ላረጀውና ዓይኖቹ ማየት ላስቸገሩት ዔሊ ዕቃዎችን ማቀበልና የመሳሰሉትን በሌሎች ዓይን ቀላል የሆነውን ነገር ሁሉ የሚሰራ ይመስለኛል። ቁ21 ላይ እንደምናየው ሐና አምስት እጥፍ አድርጎ ነው እግዚአብሄር ሲሰጣት የማየው። እግዚአብሄር የማንም ባለዕዳ እንደማይሆን የተናገረውን እውነት ያረጋግጥልኛል።
5. ልጆቹ በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ እያደረጉ የነበረውን ክፋትና በህዝቡ ላይ የሚፈጽሙትን ሁሉ ሲሰማ የወሰደው እርምጃ በጣም በለዘበ መንገድ ማነጋገር ነው። በእኔ አስተያየት ማድረግ የነበረበትና ያላደረገው ብዬ የምለው ነገር፤ በመጀመሪያ ደረጃ አነጋገሩን ስናይ እጅግ ጥንካሬ የሚያንሰውና ከዚህ በኋላ ያለውንም ውሳኔ ለእነርሱ የተወው ይመስላል። በተጨማሪም ኤሊ አባታቸው ብቻ ሳይሆን እንደሊቀ ካህን አለቃቸውም ስለሆነ ከስፍራቸው ማውረድም ነበረበት እላለሁ።
6. በተለይ ቁ29 ስንመለከት እግዚአብሄር ለሆነው ነገር ሁሉ ተጠያቂና ሃላፊ አድረጎ የያዘው አድራጊዎቹን የኤሊ ልጆች ብቻ ሳይሆን “አንተና ልጆችህ” በማለት እንደ አባትና እንደ አለቃ በሃላፊነት ላይ ተቀምጦ የነበረውን ዔሊን ጭምር እንደሆነ እናያለን።
7. እግዚአብሄር በገላትያ መልዕክት ውስጥ “አትሳቱ እግዚአብሄር አይዘበትበትም” ብሎ እንደሚናገረው የኤሊ ልጆች ምናልባትም ለብዙ ዓመታት ሲለማመዱ የኖሩት ርኩሰት እግዚአብሄር እንደማይፈርድና እንደማይቀጣ አድርገው ያዩት ይመስላል፤ ሆኖም የኤሊ ቤት ክህነቱን እንዲያጣ፣ ዘሮቹ በአጭር እንደሚቀጩ፣ ዕድሚኤአቸው ቢረዝም እንኳን የረባ ህይወት እንደማይጠብቃቸው የኤሊ ልጆችም ሁለቱ በአንድ ቀን እንደሚሞቱና ይህም ለኤሊ በምልክትነት እንደሚያገለገለው ነው የተነገረው።
8. እግዚአብሄር የሐናን ማህጸን በመከፈት ተዓምር በሰራበት ወቅት በመቅደሱ ውስጥ ያገለግሉ የነበሩት በቁ12 ላይ ምናምንቴ በማለት የሚጠራቸው ሁለቱ የኤሊ ልጆች ነበሩ። ከዚህ ልንማር የምንችለው ነገር፤ እግዚአብሄር በቤቱ ውስጥ ስለራሱ ስምና ስለ ህዝቡ ሲል ድንቅና ተአምራትን መስራቱ፤ እየተካሄደ ያለውን ርኩሰትና ዓመጽ የማጸደቁ ምልክት እንዳልሆነ የኤሊን ልጆች በማያዳግም መንገድ በመቅጣት አረጋግጧል::

## ጥናት ሶስት 1ኛ ሳሙ 3፥1-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሳሙኤል በጨቅላነቱ አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት የነበረው ሁኔታ፡ ዔሊ ቢደክምና ዓይኑ ቢፈዝም አገልግሎቱን አላቆመም ነበረ፣ የኤሊ ልጆች ገና እግዚአብሄር የተናገረው ነገር ስላልተፈጸመ በአገልግሎት ላይ ነበሩ፣ ሳሙኤልም ከዔሊ ስር ሆኖ ያገለግል ነበረ፣ በዚያ ዘመን የእግዚአብሄር ቃል ብርቅ ነበረ፣ ራዕይም አይታይም ነበረ።
2. ሳሙኤል የእግዚአብሄርን ድምጽ ለመስማት እንቢ ያለ እንቢተኛ ሰው እንዳልሆነ እግዚአብሄር ስለሚያውቅ ነው። ስለዔሊ ልጆች እግዚአብሄርን አለማወቅና፣ ስለ ሳሙኤል እግዚአብሄርን አለማወቅ የተነገሩት ሁለቱ አባባሎች የተለያዩ አስተሳሰብን እንዳዘሉ ነው የሚገባኝ፤ ምክንያቱም የነዚያ አለማወቅ ሰለእርሱ ማንነት በትክክል መረዳት ካለመፈለግና በቤቱም ውስጥ ያሉት ራሳቸውን ለማገልገል እንጂ ስለእርሱ ግድም እንደሌላቸው አይተናል። ሳሙኤል እግዚአብሄርን አለማወቁ ገና ለጋ ወጣት ስለነበረ ከእርሱ ጋራ በቂ ጊዜ አላጠፋም፣ ቁ7ትም እንደሚነግረን እግዚአብሄርም ራሱን ገና ለሳሙኤል አልገለጠለትም ነበረ።
3. በአጠቃላይ እግዚአብሄር ሳሙኤልን የጠራው አራት ጊዜ ነው። እግዚአብሄር ሳሙኤልን እየጠራው እንደሆነ ዔሊ የተገነዘበው በሶስተኛው ጥሪ ነው። እኔ እንደሚመስለኝ፤ እግዚአብሄር እርሱን ጠርቶት ቢሆን ምናልባትም በመጀመሪያው ጥሪ እግዚአብሄር እንደጠራው ለይቶ ማወቅ እንደሚችል ይመስለኛል፤ ሆኖም በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተጠራ እርሱ ሳይሆን ሌላ ሰው ስለሆነ ይህ ሰው ለሳሙኤል ሊሰማ አይችልም ብዬ ነው የማምነው።
4. ሳሙኤልን የጠራው እግዚአብሄር እንደሆነ ሲያውቅ ዔሊ ለሳሙኤል የለገሰው ምክር፤ ተመልሶ በስፍራው እንዲተኛ፣ ዳግመኛ አስቀድሞ የመጣው ዓይነት ጥሪ ከመጣ ደግሞ ማለት የሚኖርበትን ነገር መክሮ ነው ያሰናበተው። አራተኛው ጥሪ ውስጥ ያለና በሌሎቹ በሶስቱ ውስጥ ያላየሁት ነገር "እግዚአብሄርም መጥቶ በዚያ ቆመ" የሚለው ሃሳብ ነው። ከእግዚአብሄር ጋራ ባለው ጉዞ ከእኛ የተሻለ ልምድ ያላቸውን ሰዎች ምክር ለመስማት ትህትናና ክፍተት ሊኖረን እንደሚገባ እንማራለን።
5. ይህ ብላቴና ሳሙኤል መኝታ ላይ ይሁን እንጂ እውነት እንቅልፍ የሚወስደው አይመስለኝም፤ ከአሁን አሁን የእግዚአብሄርን ድምጽ እሰማለሁ በማለት በጉጉት እንደሚጠብቅ ይመስለኛል። "ባርያህ ይሰማልና ተናገር" በሚለው ሃሳብ ውስጥ ይህ "ባሪያ" የሚለው ቃል የሚነግረን፤ ሳሙኤል እግዚአብሄር ተናግሮ፣ ሳሙኤል ደግሞ ሰምቶ ነገሩ በዚያ የሚያበቃ እንዳልሆነ፤ እግዚአብሄር ያዘዘውን ወይም እንዲያደርግ የሚነግረውን ነገር ልክ ባሪያ የጌታውን ትዕዛዝ ተቀብሎ በስራ ላይ እንደሚያውል ሁሉ እርሱም ያንን ለማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን የሚገልጽ ሃሳብ ነው።
6. ሳሙኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ከእግዚአብሄር የሰማው ወይም የተቀበለው የመልዕክት ይዘታ የሚያስፈራና ወጣቱ ሳሙኤል በጭራሽ የማይጠብቀው  እንግዳ ነገር እንደሚሆንበት ይመስለኛል። ይህ የመጀመሪያ ልምምዱ የሆነው ከእግዚአብሄር የተቀበለው መልዕክት ለማስተላለፍ የሚከብድበት ምክንያት፤ በመጀመሪያ ደረጃ ዔሊ አለቃው ነው፣ እግዚአብሄርን መስማት ያስተማረው ሰው ነው፣ በእድሜም በአገልግሎትም ብዙ ልምድ ለሚበልጠው ሰው ነው የሚናገረው። ቁ14 ሲታይ እግዚአብሄር በዔሊ ቤት ላይ ያሰበውን ከማድረግ በምንም መንገድ ወደኋላ እንደማይል ያስረዳናል።
7. እኔ ከእግዚአብሄር መስማቱ ብቻ ሳይሆን የሰማው የመልዕክት ዓይነት እንቅልፍ የሚሰጠው አይመስለኝም፤ በአንድ በኩል ከእግዚአብሄር መስማቱ ውስጡን በደስታ ሲሞላው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የፍርድ መልዕክቱን ለዔሊ በምን መንገድ እንደሚነግረው በማውጣትና በማውረድ የሚቆይ ይመስለኛል። በነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናየው የሳሙኤል አገልግሎት ጠዋት ተነስቶ የእግዚአብሄርን ቤት በሮች መክፈት ነበረ።
8. በ3፥1 ላይ የምናየው እግዚአብሄር በዚያን ዘመን በጭራሽ ለህዝቡ ድምጹን እንደማያሰማና ራዕይም የሚባል ነገር የሚያይ እንዳልነበረ የሚነግረን ሲሆን፤ በ3፥19-21 ላይ ስናነብ ግን እግዚአብሄር እንደገና ለህዝቡ መናገር እንደጀመረ፣ ራሱንም በባሪያው በሳሙኤል ውስጥ ይገልጥ እንደነበረ እናነባለን።

# <u>ጥናት አራት 1ኛ ሳሙ 4፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በዚህ ቦታ ላይ “የሳሙኤል ቃል” በመባል የተነገረው ነገር፤ በ3፡21 ላይ እግዚአብሄር ለሳሙኤል ራሱን ይገልጥና በቃሉም አማካኝነት ይናገረው የነበረውን ሃሳብ ለእስራኤል ህዝብ ያስተላልፍ ስለነበረ ያንን ነው ይህ ክፍል የሚነግረን። እስራኤል ፍልስጤማውያንን ለመውጋት እንደወጡና በአቤኔዘር እንደተሰለፉ፤ ፍልስጤማውያን ደግሞ በአፌቅ እንደሰፈሩ እናነባለን። ጦርነቱ በፍልስጥኤም አሸናፊነት እስራኤል 4000 ሰዎች አጥተው እንዳለቀ ይታያል።
2. ቁጓትን ስናነብ እስራኤላውያን ለሽንፈታቸው ምክንያት ያደረጉት፤ እግዚአብሄር ራሱ በፍልስጤማውያን እንዲሸነፉ እንዳደረገ ነው የተቀበሉት። የእስራኤል አለቆች ተሰባስበው ጥያቄውን እርስ በእርሳቸው ሲወያዩበትና መልሱን ሲፈልጉ ነው የምናየው። ለሽንፈታቸው ምክንያት እግዚአብሄር ምክንያት ሆኖ ከተገኘ፤ ይህንን ጥያቄ ማቅረብ የሚገባቸው ለእግዚአብሄር ለራሱ ሊሆን እንደሚገባው ነው የሚታየኝ። ውሳኔአቸው ታቦቱን ወደጦርነት ይዞ መሄድ ሲሆን፤ እግዚአብሄር ወደ ጦርነቱ አብሮ ለመውጣት ፈቃደኛነቱ እንኳን አልተጠየቀም።
3. ከታቦቱ ጋራ የመጡት ሁለቱ የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሃስ ነበሩ። እነዚህ ሁለት ሰዎች የእግዚአብሄርን ቁርባን የሚንቁ፣ ስለ እግዚአብሄር አምልኮና ስለ እግዚአብሄር ህዝብ ምንም ዓይነት ደንታ የሌላቸው ናቸው፤ ስለዚህም እግዚአብሄር ደግሞ ለፍርድ የሚጠብቃቸው ሰዎች እንደሆኑም እናውቃለን። የዔሊ ልጆች ታቦቱን ሲያመጡ ህዝቡ በታላቅ ደስታ ሲቀበላቸው ነው የምናየው። በእኔ አመለካከት እነዚህ ሁለት ልጆች የእግዚአብሄርን መስዋዕት ያቃለሉና ህዝቡን የሚበዘብዙ ርካሽ ካህናት በመሆናቸው ከደስታ ጩኸት ይልቅ የለቅሶ ጩኸት ማሰማት ነበረባቸው እላለሁ።
4. እስራኤላውያን በታቦቱ መምጣት ደስ የተሰኙት ከጠላቶቻችን ይታደገናል በሚል እምነት ነበረ፤ ሆኖም የሚታደገው እግዚአብሄር አምላክ እንጂ ታቦቱ እንዳልነበረ አልገባቸውም። ፍልስጤማውያን ደግሞ ፍርሃት ያደረባቸው ቀድሞ እግዚአብሄር በግብጻውያን ላይ ያደረገውን ስለሚያውቁ ነበረ። ታቦቱ በዚህ ጦርነት እንዲመጣ በስብሰባና በውይይት የወሰኑት የህዝቡ አለቆች እንጂ እግዚአብሄር ታቦቱን ይዘው እንዲወጡና በዚያም ምክንያት ድል እንደሚሙቱ ስላልነገራቸው ነው።
5. የእስራኤልን በጦርነቱ መሸነፍ የሚያስተጋቡት አራት ሃሳቦች፡ ታላቅ እልቂት ሆነ፣ ከእስራኤልም ሰላሳ ሺህ እግረኛ ወታደሮች ወደቁ፣ የእግዚአብሄር ታቦት ተማረከ፣ ሁለቱም የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሃስ ተገደሉ የሚሉት ናቸው።
6. ዔሊ ከጦር ሜዳ የሚመጣውን ዜና ለመስማት በጭንቀት ይጠባበቅ የነበረው ስለ እግዚአብሄር ታቦት ጉዳይ ነበረ። ይህ ሊቀካህን እግዚአብሄር ራሱን መከላከል የማይችል አምላክ እንደሆነ ለእርሱ አስቦ ሳይሆን፤ አስቀድሞመ ታቦቱ ለጦርነት ከህዝቡ ጋራ እንዲወጣ እግዚአብሄርን ሳይጠይቅ በህዝቡ ጥያቄ ብቻ የወሰነው ውሳኔ ስለነበረ ይህ ውሳኔው ትክክል አለመሆኑን ውስጡ የተረዳ ሳይሆን እንደማይቀር እገምታለሁ።
7. የፊንሃስ ሚስት ምን አስባ ይህንን እንደተናገረች አላውቅም፤ ሆኖም እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ የእግዚአብሄር ክብር ከህዝቡ መሃል የተለየው ታቦቱ በፍልስጤማውያን በተማረከ ጊዜ ሳይሆን እነዚያ ካህናት ተብለው በቤተ መቅደስ ውስጥ የእግዚአብሄር የሆነውን ማናቸውም ቁርባኑንና መስዋዕቱን በሚያረክሱበት ጊዜ፤ በመገናኛ ድንኳን ውስጥ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋራ ዝሙት በሚፈጽሙበት ጊዜ ይመስለኛል ክብሩ የተለየው 1ኛ ሳሙ 3፡1 ላይ የምናነበውም ሃሳብ ይህንን ሃሳብ ይደግፋል ብዬ አምናለሁ።
8. ታቦቱ በመካከላቸው እያለ ሽንፈታቸው አለመቀየሩ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር፤ ድል የሚገኘው ለእግዚአብሄር በመታዘዝና ራስን አዋርዶ በንስሃ በመቅረብ፣ ርኩሰትንም ከመሃከል በማስወገድ እንጂ፤ እግዚአብሄርን ለማምለክና የእርሱን መገኘት በህይወታችን እንድንለማመድ የተሰጡንን ነገሮች በእርሱ ምትክ ቦታ መስጠታችን ሃጥያት እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል።

<u>ጥናት አምስት 1ኛ ሳሙ 5፡1-6፡21 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. የእግዚአብሄር ታቦት ራሱን ያገኘው በፍልስጤማውያን አገር በአሽዶድ ሲሆን፤ ያኖሩትም በአምላካቸው በዳጎን ቤተ ጣዖት ውስጥ ነበረ። ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ ዛሬ የሚገኝበት ሁኔታ የሚለየው፤ በአንደኛ ደረጃ ከሌላ አምላክ ከሚባል ጎን ነው የተቀመጠው፣ ሁለተኛው ደግሞ እርሱን ለማምለክ የሚመጣ ማንም የለም፣ እዚያ ያለውም እንደ እስረኛ እንጂ እንደ አምላክ አይደለም። ቁ5 ላይ እንደምናየው ምላሻቸው የማይረባ አይነት አፈ ታሪክ መፍጠር ብቻ ነበረ።
2. ቁ6 ላይ እንደምናነበው አሁን ከአምላካቸው አልፎ በህዝቡ ላይ እጁን ማክበድ ጀመረ። የፍልስጤም ህዝብ ጦርነቱን አሸንፎ ወዳገሩ ቢገባም፤ የእስራኤል አምላክ ግን እረፍትና ሰላም ሊሰጣቸው አልቻለም። ታቦቱ በምርኮ አገር ሰባት ወር በቆየበት ወቅት የጠላትን ሰፈር እያንቀጠቀጠ መሆኑን የእስራኤል ህዝብ ስለማያውቅ፤ አንዳንዱ ምናልባትም እግዚአብሄር ለማዳን የሚችል አምላክ መሆኑን በልቡ የሚጠይቅ አይጠፋም፤ ሌሎች ደግሞ ከአሁን በኋላ የሚያመልኩት አምላክ እንደማይኖራቸው አምነው ምናልባትም የራሳቸውን ልዩ አምልኮ መጀመርና፣ ሌሎች ደግሞ በተስፋ መቁረጥና በሃዘን ውስጥ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም።
3. የፍልስጤምን አምላክ ዳጎንን ሲያሰግድ፣ አምላካቸውን ብቻ ሳይሆን መላ አገሩን ለብቻው ያለምንም መሳሪያ በቁጥጥሩ ስር ሲያውል፤ ህዝቡ ራሳቸው ለጠየቁት ጥያቄያቸው መልስ አድርገው ያቀረቡት ነገር የእግዚአብሄርን ታቦት ወደመጣበት አገሩ መመለስ ነበረ። በእኔ አመለካከት ሊወስዱት የሚገባው እርምጃ "የእስራኤል አምላክ ታላቅነቱን ዳጎንንም በማንበርከክና በመስበር ስላረጋገጠልን እኛም የእስራኤልን አምላክ እናመልካለን" ማለት ይገባቸው ነበረ።
4. እነዚህ ሰዎች የገባቸው አንድ እውነት፤ በቁ3 ላይ እንደምናነበው የማያምኑበትንና የማይሰግዱለትን የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሄርን ታቦት ከመጀመሪያው ወደ አገራቸው ማምጣታቸው በደል እንደሆነ ገብቷቸዋል። እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሄር ከሚናገሯቸው ነገሮች ውስጥ፡ የእስራኤል አምላክ ክብር እንደሚገባው፣ ግብጻውያን እስራኤላውያንን የለቀቁት እግዚአብሄር በጽኑ ከቀጣቸው በኋላ እንደነበረና፣ እንደ ግብጻዊያንና እንደፈርዖን ልብን ማደንደን ጥቅም እንደሌለው ነው የተናገሩት።
5. የእግዚአብሄር ታቦት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ በእንሰሳ ላይ ወይም በአዲስም ሆነ በአሮጌ ሰረገላ ላይ ጭኖ ሳይሆን መጓጓዝ ያለበት በሌዋውያን ትከሻ ላይ ሆኖ ስለነበረ የሰጡት ምክር የሚያስቀስፋቸው ነበረ። እግዚአብሄር ህጉን የተቀበሉና እርሱ የሚፈልገውን የሚያውቁትን ሰዎች እንጂ እነዚህ ሰዎች በተረዱትና አክብሮት በመሰላቸው መንገድ ነበረ እግዚአብሄርን እያስተናገዱት የነበረው። እግዚአብሄር በምናውቀው እንጂ በማናውቀው ነገር እንደማይፈርድብን ነው እኔ የምማረው።
6. ታቦቱ ከሰባት ወራት በኋላ ተመልሶ በመምጣቱ ቁ13 እንደሚነግረን የቤትሳሚስ ሰዎች እጅግ በጣም ደስ እንደተሰኙ እናነባለን። ህዝቡ ለእግዚአብሄር የሚቃጠል መስዋዕት ለማቅረብ የተጠቀሙባቸው ነገሮች ከሞላ ጎደል የመጡት ከፍልስጤም ምድር ሲሆን፤ ማጓጓዣውን ማቃጠል ያስፈለጋቸውም ታቦቱ በሰው ትከሻ እንጂ በሰረገላ ስለማይጓጓዝ ነው።
7. የቤትሳሚስ ሰዎች ታቦቱ ውስጥ ማየት የሞከሩበት ምክንያት፤ ምናልባትም ፍልስጤማውያን ከውስጡ ያጎደሉት ነገር እንደነበረና ሁሉም ነገር በስፍራው እንዳለ ለመፈተሽ ሳይሆን አይቀርም። የቤትሳሚስ ሰዎች ከመሃላቸው አንዳንዶቹን እግዚአብሄር ሲቀስፍ በውስጣቸው የተሰማቸው ስሜትና የታያቸው ነገር፤ የሚያመልኩት አምላክ ምን ያህል ቅዱስና በአክብሮት ሊመለክ የሚገባው መሆኑ ነው።
8. በአምላካቸው በዳጎን ላይና ታቦቱ በገባባቸው ከተሞቻቸው ላይ ሁሉ ያደረገውን እያዩ፤ በተጨማሪም ይህ ሁሉ የደረሰባቸው በእጋጣሚ ሳይሆን እግዚአብሄር ራሱ ያመጣባቸው ነገር እንደሆነ በራሳቸው መንገድ ካረጋገጡ በኋላ እግዚአብሄርን ለማመለክ አለመወሰናቸው የሚያስተምረኝ ነገር፤ እግዚአብሄር የሰዎችን ዓይን ከፍቶ የወንጌልን እውነት እንዲያዩ ካላደረገ በቀር፤ ሰው በራሱ ባየው ተአምራትና በተላማመደው ነገር ራሱን ወደ እግዚአብሄር ማቅረብ እንደማይችል እማራለሁ።

## ጥናት ስድስት 1ኛ ሳሙ 7፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሳሙኤል ሊያደርግ ላሰበውና ሊወስድ ለተዘጋጀው እርምጃ ነገሮችን አቀለለለት ብዬ የማስበው ነገር የህዝቡ ልብ መዘጋጀትና እግዚአብሄርን ለመፈለግ መነሳሳታቸው ነው። በዚህ ክፍል የምንመለከታቸው የንስሃ ወይም ወደ እግዚአብሄር የመመለስ ሁለት ገጽታዎች ሆነው የምናያቸው፤ የመጀመሪያው ውስጣዊ ማለትም ራስን ለእግዚአብሄር አሳልፎ መስጠት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ውጫዊ ማለትም ሌሎችን አማልክት ከመሃከላቸው ማስወገድ ወይም ወደ እግዚአብሄር መመለሳቸውን በተግባር መግለጽ ነው።
2. ህይወታቸውን ከእግዚአብሄር ጋራ በማስተካከላቸው ከሚያገኙት በረከቶች መሃል አንዱ አድርጎ የጠቀሰው ነገር ከጠላቶቻቸው ከፍልስጤማውያን እጅ እንደሚታደጋቸው ነው።
3. እስራኤላውያን በሳሙኤል አማካኝነት ከላይ የወሰዷቸው እርምጃዎች፤ በንስሃ ወደ እግዚአብሄር መመለስ፣ ሌሎችን አማልክት ከመሃላቸው ማስወገድ፣ እግዚአብሄርን ብቻ ማምለክ፣ መጾም፣ መጸለይና ራሳቸውን ማዋረዳቸውን ሁሉ ስንመለከት እውነተኛ እግዚአብሄርን የመፈለግ ምልክት ስለሆነ፤ እግዚአብሄር ደግሞ በእውነት ለሚፈልጉኝ እገኛለሁ ስላለና በቁ3 ላይም በሳሙኤል በኩል ይህንን ሁሉ ካደረጉ ከጠላቶቻቸው እንደሚታደጋቸው ስለተናገረ ያንኑ ቃሉን ሲፈጽም ነው የምንመለከተው።
4. ከዚህ ሁኔታ መማር የምንችለው ነገር፤ ከእግዚአብሄር ጋራ ህይወታችንን አስተካክለን መጓዛችንና ከእርሱ ጋራ የቀረብን መሆናችን ጠላት እኛን ለማጥቃት ከመሞከር ወደኋላ ይላል ማለት እንዳልሆነና፣ ምናልባትም የበለጠ ጦሩን በእኛ ላይ አስከትቶ ከትክክለኛው መስመራችን ሊያስወጣን ለመሞከር እንደሚጥር ይመስለኛል።
5. ዛሬ የተገኘው ድል የመጣው እውነተኛ አምላክ የሆነውን፤ እርሱን የወከለውን ታቦቱን ሳይሆን ራሱን እግዚአብሄርን በሙሉ ልብ በማመንና በትህትና በፊቱ በመቅረብ ነው። በ1ኛ ሳሙ 4፡1-4 ላይ ስንመለከት ትኩረት የሰጡትና እንዲያድናቸው የተማመኑበት የእግዚአብሄር በህዝቡ መሃል የመገኘቱ ምልክት የሆነውን ታቦቱን ሲሆን፤ በዛሬው ክፍል 7-11 የምናየው ግን ምልክት እንዲሆን የተሰጠውን ታቦት ሳይሆን እግዚአብሄርን ራሱን በመፈለግና ራሳቸውን በማዋረድ ትኩረታቸውን በትክክለኛው ሥፍራ ላይ አድርገው እናያለን።
6. ፍልስጤማውያን ምንም እንኳን እስራኤልን ለመውጋት ጦራቸውን ያሰልፉ እንጂ ሳሙኤል መስዋዕቱን ማሳረግ እስከጀመረበት ሰዓት ድረስ ወደ እነርሱ መቅረብ አልጀመሩም ነበረ። ይህ ለእኔ የሚያስተምረኝ፤ የእግዚአብሄርን ፊት መፈለግና ከእርሱ ጋራ ያለኝን ግንኙነት ለማዳበር በምነሳበት ጊዜ የነፍሴ ጠላት ዝም ብሎ እንደማያይና እኔን ለማጥፋት የሚችለውን ሁሉ ከማድረግ እንደማይመለስ እማራለሁ።
7. ከዚህ አነጋገሩ የምረዳው፤ የጠላት ሙከራና የእግዚአብሄርን ህዝብ ለማጥቃት መሞከሩ ከዚህም በኋላ የሚቀጥልና የማይቆም ነገር እንደሆነ ሲያስገነዝብ፣ በሁለተኛ ደረጃ ሊያሳስባቸው የሚሞክረው ነገር ደግሞ፤ እስከዛሬ የረዳን እግዚአብሄር ነገንም ሊያሳልፈንና ሊረዳን የሚችለው እርሱ ስለሆነ በእርሱ በመታመን እያንዳንዱን ቀናችንን ለእርሱ በመስጠት መኖርን እንደሚኖርባቸው የሚጠቁማቸው ይመስለኛል።
8. የእስራኤል ህዝብ ሊወጓቸው የመጡትን ፍልስጤማውያንን ባዩና በፈሩ ጊዜ ያደረጉት ነገር ቢኖር ሊያድናቸውና ሊታደጋቸው የሚችለው እግዚአብሄር ብቻ እንደሆነ ስለተረዱ ሳሙኤል ወደ እግዚአብሄር እንዲጸልይላቸው ለመኑት፤ ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሄር እንደጮኸ እርሱም ጸሎቱን ሰምቶ በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንደሰጣቸው እንመለከታለን።

# ጥናት ሰባት 1ኛ ሳሙ 8፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህን ቁጥሮች ሳነብ ሳሙኤልንንና ኤሊን የሚያመሳስላቸው ነገር የሁለቱም ልጆቻቸው መስመር የለቀቁና አባቶቻቸው በሄዱበት መንገድ ያልሄዱ ልጆች እንደነበሯቸው አያለሁ። የሳሙኤል ልጆች ሹመታቸውን ወይም የነበራቸውን ሥልጣን የተጠቀሙበት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ጉቦን መቀበል፣ እንዲሁም ፍርድን በማጣመም እግዚአብሄርን የሚያሳዝኑ እንደነበሩ  ቁ3 ላይ ማየት እንችላለን።
2. ሽማግሌዎቹ ለንጉስ ጥየቃቸው ምክንያት አድርገው ያቀረቧቸው ሁለት ምክንያቶች፡ የመጀመሪያው የሳሙኤል የራሱ ሽምግልና ሲሆን ይህ ምክንያታቸው እውነት ለመሆኑ ሊያረጋግጥልን የሚችለውን ሃሳብ የምናገኘው በቁ1 ላይ “ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ” በማለት ይነግረናል። ሁለተኛ ምክንያታቸው አድርገው ያቀረቡት ሃሳብ ደግሞ የሳሙኤል ልጆች የአባታቸውን ፈለግ አለመከተል ሲሆን፤ ይህ ምክንያታቸው ደግሞ በቁ3 ላይ “ልጆቹ የአባታቸውን ፈለግ አልተከተሉም” በማለት የልጆቹን ባህርይ ይነግረናል።
3. የእስራኤልን ህዝብ በአካባቢያቸው ከነበሩት ህዝቦች ሁሉ የተለዩ የሚያደርጋቸው አንዱና ዋነኛው ነገር እንደሌሎቹ ከሰው መሃል የተመረጠ ንጉስ አለመኖሩና እግዚአብሄር እርሱ ራሱ ንጉሳቸውና መሪያቸው መሆኑ ነበረ። በዚህ ቁጥር ውስጥ ስንመለከት እስራኤላውያን ይህንን ከሌሎች ህዝቦች ልዩ ያደረጋቸውን አንዱን መለያቸውን መጣል እንደፈለጉና እንዳልተስማማቸው እንመለከታለን።
4. የሳሙኤልን ልብ ያሳዘነው ነገር የእርሱን ሽምግልና ወይም ደግሞ የልጆቹን ባህርይ በምክንያትነት መጠቀማቸው ሳይሆን፤ እግዚአብሄር ንጉሳቸው ሆኖ እያለ ሌላ ንጉስ አንግስልን የሚለው ጥያቄአቸው ነው ያሳዘነው፤ ይህንም ሲሆን ሳሙኤል የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ወደ እግዚአብሄር መጸለይ ነበረ።። ከዚህ እርምጃው በፊት ምናልባትም እኔ ብሆን የምወስደው እርምጃ የሚመስለኝ የእነርሱን ሃሳብ ለማስለወጥ ከእነርሱ ጋራ መከራከር ወይም መወያየትን የማስቀድም ይመስለኛል።
5. ይህንን የህዝቡን ጥያቄ እግዚአብሄር እንደንቀት የተመለከተበት ምክንያት፤ እንደ ሌሎች ሕዝቦች የሚመራን ንጉስ ስጠን የሚል ጥያቄ ልክ እግዚአብሄር እስከዛሬ በጥሩ ሁኔታ እንዳልመራቸውና ሌሎቹ ነገሥታት ግን ህዝቦቻቸውን ከእግዚአብሄር በተሻለ መንገድ እንደመሩ አድርገው ማየታቸው ነው እርሱን መናቃቸው። እኛ ሰዎች ስንባል ምን ያህል የቀደመውን ነገር እንደምንዘነጋና አጭር በሆነ ማስታወስ እንደምንመላለስ እመለከታለሁ።
6. እነዚህ ሰዎች ያላቸው የተሳሳተ አመለከከት ሌሎች ህዝቦች ንጉስ እንዳላቸው እንጂ እነርሱ ንጉስ እንዳላቸው አድርገው አይመለከቱም፤ ይህ ስህተት የሆነ አመለካከት የተፈጠረበት ምክንያት፤ እግዚአብሄር እንደሌሎቹ ነገሥታት የሚያዩትና ፊት ለፊታቸው ሆኖ ምሪት ሲሰጥ በአይናቸው አለማየታቸው ይመስለኛል እነርሱ ያለንጉስ እንዳልሆኑ ያስቆጠራቸው።
7. የሚያነግሱት ንጉስ የሚታወቅበት አንድ ነገር ቢኖር በመውሰድ ነው። እስከዛሬ ድረስ ይገዛቸው የነበረው እግዚአብሄር ደግሞ የሚታወቅበት ነገር ቢኖር በመስጠት ሲሆን፤ ይህንንም ያስመሰከረበት ዋነኛና ትልቁ ነገር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለዓለም መስዋዕት እንዲሆን በነጻ መስጠቱ ነው።

# ጥናት ስምንት ፲ኛ ሳሙ 9:1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመልከ ቀናነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት፣ ቁመቱ ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ ከትከሻው ዘለግ ያለ፣ ወጣት ልጅ በማለት ይነግረናል። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለሳኦል መንፈሳዊ ነገር ወይም ከእግዚአብሄር ጋራ ስለነበረው ግንኙነት የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም፤ ባብዛኛው የተነገረው ስለቁመናው ነው።
2. ሳሙኤልን ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ሃሳቦች፡ የእግዚአብሄር ሰው፣ በጣም የተከበረ፣ የተናገረው ሁሉ በትክክል የሚፈጸም ይለዋል። እነዚህ ሰዎች ወደ ሳሙኤል መሄድ ያስፈለጋቸው ምክንያት የጠፉባቸውን አህዮች ለማግኘት ስለተቸገሩና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ስለተጋቡ ነው።
3. ሳሙኤል ትልቅ የእግዚአብሄር ሰው እንደሆነና መንፈሳዊ ብቃቱን እየመሰከሩ እነርሱ ከእርሱ ሊቀበሉ የሚጠብቁት ነገር ግን ከእግዚአብሄር ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን መልካም መንፈሳዊ ስጦታ ሳይሆን ምድራዊና ታናሽ የሆነውን የአህያቸውን ነገር ነበረ። ከዚህ ሁኔታ መናገር የምንችለው ነገር፤ ሳዖልም ሆነ የሳዖል አገልጋይ መንፈሳዊ ሁኔታቸው ቀዝቃዛና እግዚአብሄርን የመፈለግ ነገር እንደማይታይባቸው መናገር እንችላለን።
4. ምንም እንኳን ሳዖል ሰለ እግዚአብሄር የሚያሳየው ምንም ዓይነት ፍላጎትና ጥማት ባናይም፤ እግዚአብሄር ግን ሳዖል ዛሬ የት እንደሚውልና የት እንደሚያድር፤ ነገ ደግሞ ሳዖል የት እንደሚገኝ አብጠርጥሮ እንደሚያውቅ እንመለከታለን። ይህ የሚያስተምረኝ በመጀመሪያ ደረጃ መንገዶቼ ከእግዚአብሄር የተሰወሩ እንዳልሆኑና መግባት መውጣቴን እንደሚያይ ሲያስተምረኝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልባቸው በእርሱ ላይ ያልሆኑትንም ሰዎች አካሄድም ሳይቀር ስለሚያውቅ ከእርሱ የተሰወረ ምንም ነገር እንደሌለ እረዳለሁ።
5. እነዚህን አመጸኛ ሰዎች እግዚአብሄር "ህዝቤ" በማለት ሲጠራቸው ነው የምንመለከተው፤ ይህንንም አባባል ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ እንገነዘባለን። ንጉሳችን አይሆንም ሌላ ንጉስ አንግስልን ብለው ለናቁት ሰዎች እግዚአብሄር እንደገና እነርሱን ከጠላቶቻቸው እጅ ለማዳን ዕቅድ ሲያወጣ እንመለከተዋለን።
6. ሳዖል በትህትና ጀምሮ በትህትና የማይጨርስ ሰው እንዳልሆነ እግዚአብሄር ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም፤ ነገር ግን እስራኤል የጠየቀውና የፈለገው ቁመናና መልክ ያለው፣ በፊታቸው ጎላ ብሎ የሚታይ፣ በጠላቶቻቸው ፊት ቢንጎራደድ ሊያስፈራራና ሊያስደነግጥ የሚችል እንጂ የልቡ ሁኔታ ደንታ ስለማይሰጣቸው እንጂ እንደ እግዚአብሄር ልብ ከሆነና ለህዝቡ ቢመርጥ ምርጫው እንደ ዳዊት ትንሽና በሰው አይን የተናቀ ሰው ሆኖ፤ በእርሱ ፊት ግን የተወደደ ሰው ነው።
7. እያንዳንዱ የጥናት ተካፋይ በውይይቱ እንዲሳተፍ ይደረግ።
8. ለእስራኤል ንጉስን ያህል ነገር ለመስጠት ሲጠቀምበት የምናየው መንገድ በሰዎች የማይጠበቅና የማንኛውም ሰው እለታዊ ተግባር በሚመስለው ነገር ውስጥ፤ ማለትም በአህያ መጥፋት ውስጥ ንጉስን ለመስጠት ሲጠቀም ነው የምናየው። በእኛም ህይወት ውስጥ እለታዊ በሆኑት ተግባሮቻችን ማለትም ለእኛ ጎልተው በማይታዩን ሁኔታዎቻችን ውስጥ እንኳን እግዚአብሄር ትልቅና አስገራሚ የሆነውን የራሱን ነገር ሊፈጽም እንደሚችል እንማራለን።

በወንድሙ ሃብተወልድ ተዘጋጀ (253) 653-4707 ethiowengel.com

# ጥናት ዘጠኝ 1ኛ ሳሙ 10፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ

1. በቁ1 ላይ ሳሙኤል ሲያደርግ የምናያቸው ሶስት ነገሮች፡ የመጀመሪያው ዘይቱን በሳዖል ራስ ላይ ማፍሰስ፣ ሁለተኛው ሳዖልን መሳምና፣ ሶስተኛው ደግሞ ለሳዖል ከእግዚአብሄር የተነገረውን መልዕክት መናገር ናቸው። በዚህ ቦታ የሳሙኤል ሳዖልን መሳም ያመለከታል ብዬ የማስበው ነገር ቢኖር፤ ሳዖል ይህንን ሃላፊነት ሲቀበል ሳሙኤልም ከእርሱ ጋራ እንደሆነ ትብብሩን መግለጡ ይመስለኛል። በህይወቱ ዘመን ህዝቡ የእግዚአብሄር እንጂ የእርሱ እንዳልሆነ እንዲያውቅ፤ እርሱ ደግሞ ባለአደራ እንጂ ባለቤት እንዳልሆነ እንዲያስታውስ የተነገረው ነው፤ ልክ ልጆች ለወላጆቻቸው፣ መንጋው ለእረኛው፣ ህዝቡ ለመሪዎቹ እንደሆኑት።
2. አንደኛው ምልክት፡ በቁ2 ላይ ሁለት ሰዎች እንደሚያገኝና የጠፉበት አህዮች እንደተገኙ የሚነግሩት መሆናቸው፤ ሁለተኛው፡ በቁ3-4 ላይ ወደ ቤቴል የሚወጡ ሶስት ሰዎች እንደሚያገኝና ሁለት ዳቦ ሰጥተውት እንደሚቀበላቸው፤ ሶስተኛው ደግሞ በቁ5 ላይ ትንቢት የሚናገሩ የነቢያት ጉባኤ እንደሚያገኝና፣ እርሱም ራሱ የእግዚአብሄር መንፈስ በሃይል እንደሚወርድበትና ትንቢት እንደሚናገር። ቅድመ ሁኔታ ሆነው የተነገሩት ከላይ ከቁ2-6 የተዘረዘሩትን ሶስት ምልክቶች (በትነን ካየናቸው ቁጥራቸው ከሶስት በላይ ነው) መሟላት ነው።
3. የተጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች፡ "የት ነበራችሁ" የሚልና፤ ሌላኛው ደግሞ "እባክህ ሳሙኤል ያለህን ንገረኝ" የሚሉ ናቸው። ሳዖል ለአጎቱ የተሟላ መልስ እንዳልሰጠ ቁ16 ግልጽ አድርጎ ይነግረናል። ሳሙኤል ለሳዖል በእስራኤል ላይ እንደሚነግስ የተናገረውን ነገር ለአጎቱ ያልተናገረበት ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ ቢችሉም፤ እኔ የሚመስለኝ ግን ሳዖል ራሱ ንግስናውን ከማወጁና ከማውራቱ በፊት እግዚአብሄር ራሱ በጊዜው ለህዝቡ እንዲገልጥና እንዲናገር የፈለገ ይመስለኛል።
4. እግዚአብሄር የምህረት አምላክ ስለሆን ህዝቡ በድለናል ብለው መንገዳቸውን የሚቀይሩበት አንድ ተጨማሪ እድል ሲሰጣቸው ነው ብዬ ነው እኔ የማምነው። ሳዖል ከመጀመሪያውም ቢሆን የእለት ተግባሩ የሆነውን የአባቱን አህዮች ፍለጋ እንጂ ንግስናን አላሰበውም፤ እነዚህንም ቁጥሮች ስናይ እንዲያውም ከንግስና መደበቅ ሲሞክር ነው የምንመለከተው፤ ስለዚህም በእኔ አመለካከት ንግስና ሳዖልን ተከትሎ አሳዶታል እንጂ ሳዖል ንግስናን ያሳደደ ሰው እንዳልሆነ ነው የምረዳው።
5. ሳሙኤል ሳዖልን ከህዝቡ ጋራ ያነጻጸረው ቁመናን አስመልክቶ ሲሆን፤ ህዝቡም ንጉሳቸውን ተመልክተው "ንጉስ ለዘላለም ይኑር" በማለት ያስጮሃቸው የሳዖል ቁመና እንደሆነ ይታወቃል። እግዚአብሄር አምላክ ለህዝቡ ቢመርጥ የተለየ የሚሆንበት ምክንያት፣ ሰው ፊትንና ቁመናን አይቶ የሚበይን ሲሆን፣ ሰው የሚያየው የውጭውንና ቁመናን፣ መልክን ሲሆን፤ እግዚአብሄር ቢሆን ግን የሰውን ልብ አይቶ ነው ምርጫ የሚያደርገው። ስለዚህም እግዚአብሄር ለህዝቡ ቢመርጥ ልብን አይቶ ስለሆነ ምናልባትም ለጊዜው ህዝቡን ያኔ የጮሁትን ያህል ላያስጮህ ይችላል፤ ይህንንም በንጉሱ ዳዊት ቁመና መመዘን እንችላለን።
6. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናገኛቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች፡ የመጀመሪያዎቹ የሳዖልን ንግስና ተቀብለው ከእርሱ ጋራ የተባበሩ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ንጉሱን ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። እኔ ከዚህ የምማረው ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሄር የቱንም ያህል ቀብቶና ግልጽ በሆነ መንገድ ሃላፊነት ቢሰጠንም እንኳን፣ በደስታ የሚቀበሉ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ እንቢ የሚሉና የማይቀበሉ ጥቂቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ መቀበል እንደሚኖርብን ነው የምማረው። ምንም እንኳን ለሚቃወሙን ሰዎች የሃይል ምላሽ መስጠት በምንችልበት ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም፤ አንዳንድ ጊዜ በቀልን ለእግዚአብሄር መተው አስፈላጊ እንደሆነ እንማራለን።
7. እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ተመቻችተውለት እያለ፤ ሳዖል እርምጃውን በትክክለኛ መንገድ ለማድረግ ዋስትና አልሆነውም፤ ይህንንም ያልኩበት ምክንያት ከዚህ በሚከተሉት ምዕራፎች እንደምንመለከተው የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ከመከተል የራሱን መንገድ የሚመርጥና፣ ሲያጠፋም በንስሃ ለመመለስ የሚከብደው ሰው ሆኖ በግልጽ እናየዋለን።
8. የሳዖል ልብ የተቀየረው ልክ ከሳሙኤል ተለይቶ ሲሄድ ነበረ፤ እኔ እንደሚመስለኝ እግዚአብሄር ሳዖል ከሳሙኤል እስኪለይ የጠበቀበት ምክንያት፤ ነብዩ ሳሙኤልም በሳዖል ህይወት ውስጥ የተጫወተውና ገና የሚጫወተው ሚና ቢኖርም እንኳን የሳዖልን ልብ ከመቀየር አንጻር እርሱ ምንም ዓይነት አስተዋጽዖ እንዳልነበረው ለሁለቱም ሊያስገነዝብ የፈለገ ይመስለኛል።

## ጥናት አስር 1ኛ ሳሙ 11፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አሞናዊው ናዖስ መጥቶ ከተማቸውን በከበባት ጊዜ የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ያደረጉት ነገር ቢኖር ከናዖስ ጋራ ቃል ኪዳን ለማድረግ መሞከር ነበረ። ይህንን ቃል ኪዳን ለማድረግ በሚጠይቁበት ጊዜ በነገሩ የተስማሙትን ሰዎች ቁጥር ይህ ክፍል ሲናገር "የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ሁሉ" በማለት ነው ያስቀመጠልን። እነዚህ ሰዎች ሊገቡበት የተስማሙት ቃል ኪዳን ያዘለው ነገር፤ የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ለአሞናዊያን ባሪያ ለመሆንና ለመገዛት ነበረ።
2. ናዖስ ለድርድራቸው ጥያቄ የሰጣቸው ምላሽ አስቀድሞ የሁሉንም ቀኝ ዓይን አውጥቶ እነርሱን ብቻ ሳይሆን እስራኤልን ሁሉ ካዋረደ በኋላ ቃል ኪዳን እንደሚገባ ነበረ የመለሰው። በእኔ አመለካከት ናዖስ የዚህ ዓይነቱን ከባድና አስጨናቂ የሆነ ጥያቄ እንዲጠይቅ የልብ ልብ የሰጠው ነገር አስቀድመው ለመገዛት በፈቃደኛነት እጃቸውን በመስጠታቸው ነው። እኛም ብንሆን ከሰይጣን ጋራ ድርድር ከጀመርንና እንድ እርምጃ በህይወታችን ሥፍራ ከሰጠነው በዚያ ብቻ እንደሚቆም አድርገን ማሰብ ሞኝነት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል። ኤፌ 4፡27 ከዚህ ሃሳብ ጋራ አብሮ ሊሄድ ስለሚችል ቢነበብ ይረዳል።
3. አሞናዊው ናዖስ በነገሩ እየከፋና እያከረረ መምጣቱ የኢያቢስ ሰዎች እርዳታ ለመፈለግ ወደ ወንድሞቻቸው መልዕክት ሲልኩ ነው የምንመለከተው። የኢያቢስን ሰዎች ለማጥቃት የመጣው ጠላት የእነርሱ ጠላት ብቻ ሳይሆን እስራኤል ሁሉ ለማዋረድ የተነሳ ጠላት እንደሆነ ሁሉ፤ የእኛ ጠላት ሰይጣንም የአንዳችንን ብቻ ሳይሆን የሁላችንን ውድቀትና ሞት የሚመኝ መሆኑን በመረዳት እጅ ለእጅ ተያይዘን የምንዋጋው ጠላት መሆኑን ከዚህ ታሪክ መማር እንችላለን።
4. መልዕክተኞቹ ያመጡትን ዜና የሰማው ህዝብ ሁሉ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዳለቀሰ እናነባለን። ሳዖል ከኢያቢስ ሰዎች የመጣውን ዜና በሰማ ጊዜ የእግዚአብሄር መንፈስ በሃይል እንደወረደበትና እጅግ እንደተቆጣ በቁ6 ላይ እንመለከታለን። በዚህን ጊዜ የወሰደው እርምጃ ከህዝቡ መሃል አንዳችም ሰው ሳይቀር ሳዖልን ለጦርነት ተከትሎ እንዲወጣ አዋጅ በማስነገር ህዝቡን ለጦርነት እንዳዘጋጀ ነው የምንመለከተው።
5. መልዕክተኞቹ ያመጡላቸው መልዕክት ነገ ጸሐይ ሞቅ ሲል ነጻ እንደሚወጡ የሚናገር ሲሆን፤ ህዝቡ ይህንን በሰማ ጊዜ ስሜቱን የገለጠው እጅግ ታላቅ በሆነ ደስታ በመፈንደቅ ነበረ።
6. እግዚአብሄር ይህንን ጦርነት ተጠቅሞ የሰራው የሚታየኝ ነገር፤ በህዝቡ ልብ ሳዖል ሙሉ ተቀባይነት እንዲያገኝና እንዲሁም ቀድሞ ለመገዛት እንቢ ይሉ የነበሩት እንኳን ቢሆኑ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራች መንገድ እንደዘጋባቸው እመለከታለሁ። ሳዖል ንግሥናውን በመልካም አጀማመር እንደጀመረ የሚጠቁመን በቁ13 ላይ በተቃዋሚዎቹ መገደል ለመስማማት እንቢ ማለቱ፤ በተጨማሪም ደግሞ ለድሉ ምክንያት እርሱ ሳይሆን እግዚአብሄር መሆኑን መቀበሉ መልካም አጀማመር እንደጀመረ ያሳየኛል።
7. በእግዚአብሄር ዘንድ መቀባቱን፣ በአብዛኛውም ህዝብ ደግሞ ተቀባየነት ያገኘ መሆኑን እናውቃለን፤ ሆኖም ንግስናውን ለመቀበል ያልፈለጉ፣ ሳዖል በጦርነት ህዝቡን ማዳን የሚችል መሆኑን ሙሉ ለሙሉ መቀበል ያልቻሉ ሰዎች እንደነበሩም ተመልክተናል። ንግስናው በብዙዎች ብቻ ሳይሆን አሁን በጦርነትም ተፈትኖ ያለፈ ስለሆነ ህዝቡ ሁሉ ለመቀበል ስለማይቸገሩ በአንድ ልብ ከእርሱ ጋራ ህዝቡ ሁሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገ ሥርዓት እንደሆነ እገምታለሁ።
8. እግዚአብሄር ሁልጊዜ በአንድ አይነት መንገድ ብቻ ነው የሚሰራው ብሎ ማሰብ የተሳሳተ አመለካከት ነው፤ እርሱ አምላክ ስለሆነና ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ፣ መቼ ምን አይነት ትዕዛዝ መስጠት እንደሚኖርበት የሚያውቅ ስለሆነ ሁልጊዜ በአንድ መንገድ ብቻ የሚሄድና በአንድ አይነት መንገድ ብቻ የሚሰራ አምላክ አይደለምና ነው።

# ጥናት አስራ አንድ 1ኛ ሳሙ 12፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ1-7 ያለውን የሳሙኤልን ንግግር በአንድ አረፍተ ነገር ለመጠቅለል “የተሰጠኝን አገልግሎት በሚገባ ተወጠቻለሁ” ወይም እንደ ጳውሎስ “አገልግሎቴን ፈጽሜአለሁ” ማለት እንችላለን። ሳሙኤል ስላገለገለው አግልግሎት ራሱን የገመገመውን ህዝቡ ትክክለኛ ግምጋሜ እንደሆነ እንደተቀበሉት በቁ4 ላይ ከተናገሩት ምላሻቸው ማየት ይቻላል።
2. ከባርነቱና ከመከራው ነጻ ለመውጣት ህዝቡ ጩኸቱን ወደ እግዚአብሄር ማሰማት ነበረበት። ህዝቡ ወደ እግዚአብሄር በጮኸ ጊዜ እግዚአብሄር መልስና መፍትሄ አድርጎ የተጠቀመው ነገር ቢኖር ሁለት ሰዎችን ማለትም ሙሴንና አሮንን መላክ ነበረ።
3. የረሱት ህዝቦቹ መልሰው እንዲያስታውሱትና ወደ እርሱ እንዲመለሱ እግዚአብሄር የተጠቀመበት መንገድ በአካባቢው የሚኖሩትን መንግሥታት እነ ፍልስጤምና ሞዓብን ጠላት አድርጎ በማስነሳት ነው። በአሊምንና አስታሮትን እንዳመለኩ፤ አሁን ከጠላቶቻቸው ቢታደጋቸው ግን እርሱን እንደሚያመልኩ ነው ቃል የገቡለት። ይህንን ቃል ኪዳን ሲገቡ እግዚአብሄር ደግሞ እንደእነ ይሩበአል፣ ባርቅ፣ ዮፍታሄና ሳሙኤልን የመሳሰሉ መሳፍንቶች በማስነሳት ከጠላቶቻቸው ታደጋቸው።
4. የመሳፍንቶቹ ቁጥር መብዛት የሚያሳየን ነገር ቢኖር፤ አንተን ብቻ እናመልካለን በማለት ቃል ኪዳን የገቡት ህዝቦች ቃል ኪዳናቸውን እንዳልጠበቁ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ ቃላቸውን ጠብቀው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሄርን ይህንን ያህል ጊዜ በጠላቶቻቸው እጅ ባልሰጣቸውና መልሶም አዳኝ ባላዘጋጀላቸው ነበረ። ከዚህ ሁኔታ ስለስው ባህርይ የምንማረው ቃል የገባውን በራሱ መጠበቅ እንደማይችልና፤ ስለ እግዚአብሄር የምንማረው ደግሞ ትዕግሥተኛነቱንና የይቅርታውን ብዛት ነው።
5. ከአምላካቸው ጋራ በሰላም እንዲኖሩና መልካም እንዲሆንላቸው የሚፈልጉ ከሆነ እነርሱና ንጉሳቸው ሊያደርጓቸው የሚገባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡ እግዚአብሄርን መፍራት፣ እግዚአብሄርን ማምለክ፣ እግዚአብሄርን መታዘዝ፣ በእግዚአብሄር ትዕዛዝ ላይ አለማመጽ፣ አምላካቸውን እግዚአብሄርን መከተል ናቸው። ይህንን ብታደርግ ይህ የሆንልሃል፤ ይህንን ባታደርግ ደግሞ ይህ ይመጣብሃል የሚል ከሁኔታ ጋራ የተያያዘ ስለሆነ “ሁኔታዊ ቃል ኪዳን” ወይም ደግሞ በእንግሊዝኛ “conditional promise” ይባላል።
6. ሳሙኤል ይህንን ተአምር በማድረግ የእስራኤል ህዝብ እግዚአብሄርን እንደ ንጉሳቸው አድርገው ከመቀበል ይልቅ ሌላ ንጉስ እንዲነግስላቸው መጠየቃቸው በእግዚአብሄር ፊት ምን ያህል በደል እንደሆነና እርሱን እንዳስከፋው ለማሳየት እንደሆነ እናነባለን። እኔ ከቁ19 ላይ የምመለከተው ህዝቡ እግዚአብሄር በዚህ ምክንያት እንዳይገላቸው የመፍራትን ነገር እንጂ እርሱን ባደረጉት ነገር ተጸጽተው እግዚአብሄርን የማሳዘናቸው ነገር ላይ ያተኮሩ ሆኖ አይታየኝም።
7. ሳሙኤል ህዝቡን አትፍሩ እያለ ሲያጽናና ያደረጉትን ሃጥያታቸውንና ክፋታቸውን እየሸፋፈነላቸው አይደለም፤ ይህንንም ማለት የቻልኩበት ምክንያት በዚሁ ቁጥር ላይ ስናነብ “ይህንን ሁሉ ክፋት አድርጋችኋል” እያለ አንዱን ሃጥያታቸውን ብቻ ሳይሆን ብዙውን በማንሳት ያስታውሳቸዋል። ሳሙኤል የሰጣቸው ሁለት ምክሮች፡ አንደኛው እግዚአብሄር በፍጹም ልባቸው እንዲያመልኩት እንጂ እርሱን ከመከተል ፈቀቅ እንዳይሉ፤ ሁለተኛው ደግሞ ሊጠቅሟቸውና ሊያድኗቸው የማይችሉትን ምናምንቴ ነገሮች እንዳይከተሉ ወይም እንዳያመልኩ ነው።
8. “የራሱ ህዝብ ያደርጋችሁ ዘንድ ስለወደደ” የሚለው አነጋገር እስራኤል ህዝቡ ሊሆን የቻለው ከእግዚአብሄር ፍቅር የተነሳ እንደሆነ ይታያል፤ በተጨማሪ ደግሞ እግዚአብሄር ህዝቡን ስለማይተውበት ምክንያት ሲነግረን፤ የማይተውበት ምክንያት ከታላቅ ስሙ የተነሳ እንደሆነም ያስረዳናል።

## ጥናት አስራ ሁለት 1ኛ ሳሙ 13፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በንጉሳቸው በሳኦል አማካኝነት ከተያዙበት ባርነት ለመላቀቅ ውሳኔ አድርገው እስከተነሱ ድረስ ፍልስጤማውያን ያለምንም ችግር ይኖሩ እንደነበረና ነገር ግን ለባርነት እንቢ አሻፈረኝ ባሉ ጊዜ ግን፤ ቁ4 ላይ እንደሚነግረን እስራኤል በጠላቷ በፍልስጤም ዘንድ እንደ ርኩስ ተቆጥራ እንደተጠላችና ጠላታቸው ባለና በሌለ ሃይሉ እንደተነሳባቸው እናነባለን። እኛም ከዚህ የምንማረው ነገር ቢኖር፤ ለእግዚአብሄር መንግስት የሚሆን ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እስካላደረግን ድረስ ጠላታችን አይነካካንም፤ ሆኖም ተነስተን ለጌታ መንግስት እንሰራለን ብለን ስንነሳ ግን ጠላታችን ያለ የሌለ ሃይሉን አስከትቶ እንደሚነሳብን መረዳት ይኖርብናል።
2. በቁ5-7 ላይ የምንመለከተው ነገር ጦርነታቸውን እንዲዋጋላቸውና በፊታቸው እንዲሄድ ጠይቀው የተቀበሉት ንጉስ በእርግጥም ለጦርነት አብሯቸው ወጥቷል፤ ሆኖም ግን እነርሱ እንዳሰቡትና እንደጠበቁት የድልን ውጤት ሊያስገኝላቸው አልቻለም። ከዚህ ሁኔታ ለእነዚህ ሰዎች ሊያረጋግጥ የቻለው አንድ እውነት በፊታቸው የሚወጣ ንጉስ አላቸው ማለት በጦርነት ጊዜ ድል አድራጊዎች ይሆናሉ ማለት እንዳልሆነ ነው። ይህ ለእኛ የሚያስተምረን ቢኖር፤ ማናቸውም የጠየቅነውና የፈለግነው ነገር ቢሟላልን እንኳን ያለ እግዚአብሄር ከንቱ መሆኑን ነው።
3. እነዚህ ሰዎች ያዩት ነገር የጠላታቸው የፍልስጤም ሰራዊት የቁጥሩን ብዛት እነርሱ ካሰለፉትና በቁ2 ላይ ከምናነበው ከሶስት ሺህ ሰራዊት ጋራ ሲያነጻጽሩት ያ ነበረ ልባቸውን ያቀለጠው። በዚያን ሰዓት ህዝቡ ያደረገው ነገር ምን እንደነበረ ከቁ6-7 ላይ ማንበብ ይቻላል፤ በየዋሻው፣ በየቁጥቋጦው፣ በየዓለቱ መካከል፣ በየገደሉ፣ በየጉድጓዱ ሁሉ መደበቅና እንዲያውም አንዳንዶቹ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ጋድና ወደገለዓድ ምድር እንደገቡ እናነባለን።
4. በቁ4 ላይ ህዝቡ ፍልስጤማውያን ምን ሊያደርጉ እንዳሰቡና ጦርነቱ ወዴት እንደሚያመራ ገና የተመለከቱት ነገር ስላልነበረ ንጉሳቸውን መከተልና መደገፍ አልተቸገሩም ነበረ፤ ሆኖም ከቁ5 ጀምሮ ጠላቶቻቸው በምን ዓይነት አመጣጥ እንደመጡና የሰራዊታቸውን ብዛት በተመለከቱ ጊዜ ግን ከንጉሳቸው ጋራ መቆም የሚያዋጣቸው ነገር ሆኖ ስላላዩት የመረጡት ምርጫ ቁ6-8 እንደሚነግረን ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች መበተን ነበረ። ነገሮች እስከሚከፉና እስከሚከብዱ ድረስ ተከታይ እንደማይጠፉ፤ ሆኖም ሁኔታዎች ሲከፉ ጸንቶ በነበሩበት የሚገኙ ሰዎች ብዙ እንደማይሆኑ ማየት ይቻላል።
5. ሳኦል ለእርሱ ያልሆነውንና የማይገባውን መስዋዕት መፈጸም የተገደደበት ምክንያት፤ በተለይ ቁ11ድን ስናይ ሳሙኤል በቀጠረው ቀጠሮ አለመምጣቱ፣ ሰራዊቱ መበታተኑና፣ ፍልስጤማውያን ደገሞ በማክማስ መሰብሰባቸውን ስላየ ነበረ የሚቃጠለውን መስዋዕት ለማቅረብ የወሰነው። ሳኦል መስዋዕቱን አቅርቦ እንደጨረሰ ወዲያውኑ ሳሙኤል እንደመጣ ክፍሉ ይነግረናል። ሳኦል አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ የራሱን መፍትሄ እንደወሰደ ሲታይ፤ ኢዮሳፍጥ ግን በቀጥታ ችግሩን ከራሱ ጫንቃ ላይ አንስቶ በእግዚአብሄር ጫንቃ ላይ በማኖር ነበረ አስደናቂ መፍትሄን ያገኘው።
6. በሳኦል አመለካከት ቁ12 መጨረሻ ላይ እንደሚናገረው መስዋዕት ማቅረቡ ለእርሱ የግድ እንደነበር ሲያስብ፤ ሳሙኤል ደግሞ በቁ13 ላይ ከሚናገረው ሳኦል የማይገባውን ነገር እንዳደረገና፣ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ እንዳልጠበቀ አድርጎ ነው የሚናገረው። ሳኦል የወሰደው እርምጃ በህይወቱ ላይ ያስከተለው ነገር በቁ13-14 ላይ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ጠብቆ ቢሆን መንግሥቱ ይጸና እንደነበረ፤ አሁን ግን ይህንን ስላደረገ መንግሥቱ እንደማይጸና ነው በሳሙኤል በኩል የተነገረው።
7. እስራኤል በፍልስጤም ባርነት ሥር እንዲቆይ ጠላታቸው የተጠቀመበት ታክቲክ በቁ19 እና 22 ላይ እንደምንመለከተው ከእስራኤላውያም መካከል ማንም የጦር ዕቃ እንዳይኖረው በማድረግ ነበረ። ጳውሎስ በኤፌሶን 6፡11 ላይ "የዲያቢሎስን የተንኮል ሥራ መቃወም ትችሉ ዘንድ፤ የእግዚአብሄርን የጦር ዕቃ ልበሱ።" በማለት ነው ክርስትያኖችን የሚመክረው።
8. ሁኔታዎችን በሥጋዊ ዓይኖቻችን ማየት ሁልጊዜ የሚያስከትለው ነገር ፍርሃትና አለማመን ስለሆነ፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን በተለይም በ2ኛ ነገ 6 ላይ የሚሰጠን መፍትሄ እግዚአብሄር የልብ ዓይኖቻችንን ከፍቶልን ማየት እንድንችል መጸለይን ነው።

## ጥናት አስራ ሶስት 1ኛ ሳሙ 14፡1-52 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እስራኤል በዚህ በነበሩበት ሁኔታ ማለትም የጦር እቃ በሁለት ሰዎች እጅ ብቻ በሚገኝበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ጦርነቱን ለማሸነፍ የማይታሰብ ነገር እንደሆነ ለማንም ሰው ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ምክንያቱን አይነግረንም፤ እኔ ሳስበው አባቱ በፍርሃት እንደተያዘና በእግዚአብሄር ላይ ምንም ዓይነት የእምነት እርምጃ የማይታይበት በመሆኑ ዮናታን ያሰበውን ሃሳብ ቢነግረው የእርሱንም እምነት ሊያኮላሽበት እንደሚችል ስለተረዳ ይመስለኛል።
2. ዮናታን ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ሆኖ ለጋሻ ጃግሬው ማስተላለፍ የፈለገው እውነት እግዚአብሄር በብዙም ሆነ በጥቂት የማዳን ችሎታ እንዳለው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ለእኔ እንደገባኝ ከሆነ ዮናታ በዚህ ጊዜ እግዚአብሄር በዮናታንና በሎሌው በኩል ፍልስጤምን ለመምታትና በነርሱ በኩል ድል ለመስጠት ፈቃዱ መሆኑን የተረዳ አይመስልም፤ ይህንንም ማለት ያስቻለኝ "ምናልባት" የሚለው አነጋገሩ ነው። ም ቢሆን የሚያውቀው ነገር እንዳልሆነ ይመስላል በተለይም "ምናልባት" የሚለው አብባሉ ይህንን እውነት የሚጠቁመን ይመስለኛል።
3. በቁ6 ላይ ከተናገረው አነጋገሩ ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሄር በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን ሊያደርግ እንዳሰበ ዮናታ በወቅቱ የተረዳ እንዳልነበረ ብለናል፤ ሆኖም በተከታዮቹ ቁጥሮች ውስጥ ይህ ሰው እግዚአብሄር እውነትም ድል ሊሰጣቸው ፈቃደኛ እንደነበረ ማወቁን እንረዳለን፤ ይህንንም ለመረዳት የተጠቀመበት መንገድ በቁ9-10 ላይ ለራሱ ባዘጋጀው ምልክት ነው። ዮናታን በርሱና በጋሻ ጃግሬው ተጠቅሞ ህዝቡን እንደሚያድን እርግጠኛነቱን የተናገረው በቁ12 ላይ ነው።
4. የመጀመሪያው ቡድን ሳዖልና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሰዎች ናቸው፤ ሁለተኛው ቡድን ቀድሞ ከፍልስጤማውያን ጎን ተሰልፈው የነበሩና አብረዋቸው ወደ ሰፈራቸው የወጡ ዕብራዊያን፤ ሶስተኛው ቡድን ደግሞ በኮረብታማው በኤፍሬም ሃገር ተሸሽገው የነበሩ እስራኤላውያን በማለት ይከፋፍላቸዋል።
5. ቁ 24 ህዝቡ ተጨንቆ ነበረ፣ ቁ28 ህዝቡ ተዳክሞ ነበረ፣ ህዝቡ እጅግ ዝሎ ነበረ። ለዚ ሁሉ ምክንያት ሆኖ በዚህ ክፍል ውስጥ የምናየው ሰው ሳዖል ነው፤ ምክንያቱም ህዝቡ በጦርነት ላይ እያለ ምግብ በልቶ እንዳይበረታና ጠላቶቹን እንዳይበቀል ዮናታንም ሆነ ህዝቡ ያልተቀበሉት ዓይነት ጾምን በማወጅ በህዝቡ ላይ ለተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ምክንያት መሆኑን እናያለን። ዮናታን ስለሁኔታ የሰጠው አስተያየት አባቱ ልክ እንዳልሆነና ጦርነቱ ከዚህ በላይ ስኬታማ እንዳይሆን አስተዋጽዖ እንዳደረገ ተናግሯል።
6. የመጀመሪያው የንጉሱ የሳዖል ሲሆን አሁኑኑ ተከትለናቸው እንውጣና እስኪነጋ ድረስ እንበዝብዛቸው የሚል አመለካከት ነው። ሁለተኛው ዓይነት አመለካከት ማናቸውንም ንጉሱ የሰነዘረውን ሃሳብ ተቀብሎ ለመንቀሳቀስ ዝግጁ የሆነ ህዝብ ሲሆን ይህ ክፍል በቁጥር አብዛኛውን የያዘ ነው። ሶስተኛውን ዓመለካከት የያዘው አንድ ሰው ብቻ ነው የእርሱ ሃሳብ እግዚአብሄርን እንጠይቅ የሚል ነው።
7. ዮናታን መገደል አይኖርበትም ብለው ህዝቡ ለሳዖል ተቃውሞ ያሰሙባቸው ሁለት ምክንያቶች፡ የመጀመሪያው ለእስራኤል ታላቅ ድልን ማስገኘቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፤ ይህንን ለእስራኤል ያስገኘውን ድል ያስገኘው በእግዚአብሄር እርዳታ መሆኑ ነው። በእግዚአብሄር እርዳታ ድሉን ማስገኘቱ በምክንያትነት የተጠቀሰበት ምክንያት፤ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱና እግዚአብሄር በእርሱ በኩል ለህዝቡ ደህንነትን ለማምጣት መወሰኑ ሃጥያት በእርሱ ፊት እንዳልሆነበት ለማሳየት እንደሚሞከሩ ነው ለእኔ የሚገባኝ።
8. በፍርሃትና በመሸነፍ ተውጦ የነበረው የእግዚአብሄር ህዝብ እንደገና ተነቃቅቶ ጠላቱን ማሳደድ እንዲጀምር ለማድረግ ምክንያት የሆነው ዋነኛው ሰው የሳዖል ልጅ ዮናታን ነው።

## ጥናት አስራ አራት 1ኛ ሳሙ 15፡1-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እግዚአብሄር በዚህ ሥፍራ ላይ አማሌቅን ጨርሶ ለማጥፋት የወሰነበትን ምክንያት በቁ2 ላይ ስናነብ እስራኤል እግዚአብሄር የተስፋ ቃል ወደገባላቸው ምድር በሚጓዙበት ወቅት በመንገዳቸው ላይ ቆሞ ስለተቃወማቸው ነው። የእግዚአብሄር ትዕዛዝ የማያሻማና ቀጥተኛ ነበር ማለት የሚቻልበት ምክንያት በቁ3 ላይ ምን ምን ማድረግ እንደሚኖርበት በመዘርዘር የተናገረውን ስናይ አሻሚ የሆነ ነገር የለውም።
2. አማሌቃውያን እስራኤልን ወደ ተስፋይቱ ምድራቸው እንዳይገቡ በመንገዳቸው እንቅፋት ያቆሙ ሲሆን፤ ቄናውያን ደግሞ በሌላ አንጻሩ ለእስራኤል በጉዟቸው ቸርነትን ያደረጉ ሕዝቦች እንደሆኑ ቁ6 ያሳየናል። የአማሌቃውያን እድል ፈንታ እንዳይደርስባቸው ከፈለጉ ቄናውያን ማድረግ የነበረባቸው ነገር ከዓማሌቃውያን አካባቢ መራቅ ነበረ።
3. የሳዖል የመጀመሪያ አለመታዘዝ ሆኖ የምናነበው ነገር በቁ8 ላይ የአማሌቅን ነጉስ አጋገን በምርኮኛነት ማምጣቱ ነበረ። ሳዖል መጥፋት አለባቸው ብሎ በራሱ የወሰናቸው የተናቁና የማይጠቅሙ ብሎ ያሰባቸውን ሲሆን፤ እንዳይጠፉ የወሰነው ደግሞ ምርጥ ምርጥ የሆኑ፣ የሰቡና፣ መልካም ሆነው የታዩትን ሁሉ ነው። ንጉሱ ሳኦል አለመታዘዙ ካለማወቅ የተነሳ እንዳልነበረ የሚያስገነዝበን በቁ9 ላይ የምናነበው “እነዚህን ፈጽመው ለማጥፋት ፈቃደኞች አልነበሩም” የሚለው ሃሳብ ነው።
4. ቁ12 ላይ የምናየው ለራሱ ክብር የመታሰቢያ ሃውልት ሲሰራ ነው። ይህንን ለማድረግ ያበቃው ምናልባትም ንጉሱን አጋግ ለመማረክና በእጁ ለማስገባት በመቻሉ ሳይሆን አይቀርም ብዬ አስባለሁ።አዎን! እግዚአብሄርና ሳዖል በሚናገሩት ነገር ልዩነት ይታየኛል፤ የሚታየኝ ልዩነት እግዚአብሄር ሳዖል ትዕዛዜን አልፈጸመም በማለት ሲናገር፣ ሳዖል ደግሞ በአንጻሩ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ፈጽሜአለሁ በማለት ተቃራኒ ነገር ነው የሚነግረው።
5. ሳዖል ትክክል እንዳልተደረገ በገባውና እግዚአብሄርን አለመታዘዝ ሆኖ ባየው ነገሮች ሁሉ ራሱን ሳያስገባ ተጠያቂ አድርጎ ለሳሙኤል የተናገረው ሰራዊቱ ይህንን እንዳደረገ አድርጎ “...ማርከው ያመጧቸው” “...ሳይገድሉ የተዉአቸው” በማለት የሚናገር ሲሆን፤ መልካም መስሎ የታየውንና እግዚአብሄርን መታዘዝ አድርጎ ባሰበው ነገር ውስጥ ግን ራሱን በማስገባት “...በሙሉ አጥፍተናል” በማለት ሲናገር ነው የምናየው።
6. ሳዖል እግዚአብሄርን እንዲበድል የነዳው ነገር በቁ19 ላይ እንደምንመለከተው ስግብግብነቱ እንደሆነ ከሳሙኤል የተግሳጽ አነጋገር እንረዳለን። እግዚአብሄር በሚቃጠል ቁርባንና መስዋዕት ደስ አይሰኝም ማለት ሳይሆን፤ ሳሙኤል ሊናገር የፈለገው ነገር ምንም እንኳን የሚቃጠል ቁርባንና መስዋዕት እግዚአብሄር ያዘዘውና የሚፈልገው ነገር ቢሆን፤ የእርሱን ትዕዛዝ ማክበርና መታዘዝ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር እንደሆነ ለማስረዳት ነው።
7. ሳሙኤል የተጠቀመባቸው ሁለቱ አረፍተ ነገሮች “አንተ የእግዚአብሄርን ቃል ንቀሃል” እና “እግዚአብሄርም በእስራኤል ላይ ንጉስ እንዳትሆን ንቆሃል” የሚሉት ናቸው። ሳዖል በቁ30 ላይ እንደምናነበው ንስሃ የሚገባውና የሚናዘዘው ሳሙኤልም አብሮት እንዲሆን የሚፈልገው በህዝቡ ፊት ክብር ያለው ሆኖ ለመታየት መሆኑን ከራሱ አንደበት እንሰማለን።
8. በዚህ ሥፍራም ሳዖል እንደለመደው ሃጥያቱን በሰዎች ላይ ለማላከክ መሞከሩን ስንመለከት በተለይም ደግሞ እርሱ የእስራኤል ንጉስ ሆኖ እያለ ከሥሩ ያለውን ህዝብ ፈርቼ ይህንን አደረግሁ የሚለው አነጋገር በእኔ አመለካከት ሰንካላና ተቀባይነት የሌለው ምክንያት እንደሆነ ማንም ሰው የሚያውቀው ሲሆን፤ እግዚአብሄርም ቢሆን ሳዖል ባቀነባበረው ምክንያት እንዳልማረከውና በእርሱ ዘንድ እንደተናቀ መሆኑን ክፍሉ አስረግጦልናል።

# ጥናት አስራ አምስት 1ኛ ሳሙ 16፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ሳሙኤልን ያነጋገረባቸው ሁለት ርዕሶች፤ የመጀመሪያው ለሳኦል እያደረገ ባለው ነገር ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በአዲሱ የእግዚአብሄር የንጉስ ምርጫ ላይ ያተኮረ ነበረ። ከነዚህ መሃል ለሳሙኤል አጠያያቂ ሆኖ የተገኘው ርዕስ ሁለተኛ ማለትም አዲስ ንጉስ እንዲቀባ የተሰጠው ትዕዛዝ ነው። እግዚአብሄር የሳሙኤልን ፍርሃት ሰምቶ ስለፍርሃቱ መገሰጽ ሳይሆን መፍትሄውን ነው ሲሰጠው የምናየው።
2. ሳሙኤል ቀንዱን ሞልቶ ንጉስ ለመቀባት ሲሄድ ለተልዕኮው መከናወን ማወቅ ከሚያስፈልገው ነገሮች መሃል የተነገረው አንድ ነገር ቢኖር፤ እሴይን ወደ መስዋዕቱ እንዲጠራ ነው። ቁ3 ላይ "...ከዚያም የምታደርገውን አሳይሃለሁ" በማለት ሳሙኤል የመጀመሪያውን ትዕዛዝ ሲታዘዝና በዚያ ታማኝ ሆኖ ሲገኝ የሚቀጥለውን እንደሚያሳየው አምኖ ነው ጉዞውን የቀጠለው። እኔ ከዚህ የምማረው ነገር፤ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር በጊዜው የሚያስፈልገንን ነግሮን የወደፊቱን ወይም የሚቀጥለውን እርምጃችንን በእምነት መራመድ እንደሚኖርብን ሊያደርግ እንደሚችል እማራለሁ።
3. በ1ኛ ሳሙ 9፡2 ላይ እንደምንመለከተው ነብዩ ሳሙኤል የመጀመሪያውን ንጉስ ሳኦልን ሲቀባ በቁመናውና በመልኩ ከሌሎች የማይተናነሰውን ሰው የቀባ ስለሆነ ዛሬም እግዚአብሄር በዚያንው አይነት እንደሚሄድ ስላሰበ ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ይህ ክፍል በእግዚአብሄርና በሰው አመለካከት መሃል ያለውን ልዩነት ሲያሰፍር፤ "ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፤ እግዚአብሄር ግን ልብን ያያል" በማለት ይነግረናል።
4. ከዚህ ክፍል የምንረዳው እሴይ ዳዊትን ጨምሮ ስምንት ልጆች እንደነበሩት ነው። እሴይ ልጁን ዳዊትን ለሳሙኤል ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ሃሳቦች፤ አንደኛው ዳዊት የሁሉም ታናሽ እንደነበረ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሥራው የበግ ጠባቂነት እንደሆነና አሁንም ያንኑ እያደረገ እንደሆነ ነው። ምንም እንኳን የዳዊት ታናሽነትና እረኝነት እየተነገረው እርሱ እስኪመጣ አንቀመጥም ማለቱ አምላክ የውስጥን ስለሆነ የሚመለከተው ታናሽነቱም ሆነ እረኝነቱ ከመቀባት እንደማያግደው ተረድቷል ማለት ነው።
5. ሳኦል በክፉ መንፈስ መጨነቅ የጀመረበትን ሁኔታ ቁ14 ሲነግረን "የእግዚአብሄር መንፈስ ከሳኦል ስለራቀ" በማለት ምክንያቱን በግልጽ ያስቀምጥልናል። አገልጋዮቹ መፍትሄ አድርገው ያቀረቡለት በገና ደርዳሪ እንዲያስመጣ ነበረ፤ ይህ መፍትሄ ዘላቂነት የማይኖረው ምክንያት በየጊዜው በገና ደርዳሪ መጠራት ሊያስፈልገው ነው፤ ነገር ግን ከእርሱ የራቀው የእግዚአብሄር መንፈስ ወደ እርሱ እንዲመለስ ህይወቱን ከእግዚአብሄር ጋራ ማስታረቅ ትክክለኛው መፍትሄ ሊሆን ይገባ ነበረ።
6. መልካም አድርጎ በገና መደርደር እንደሚችል፣ ጀግናና ተዋጊ እንደሆነ፣ በአነጋገሩ አስተዋይ እንደሆነ፣ የደስ ደስ ያለው ልጅ እንደሆነና፣ በመጨረሻም እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ እንደነበረ ነው የተናገረው። ስለዳዊት የተነገሩት ሁሉም መልካምና በጎ ነገሮች እንደሆኑ ቢታወቅም፤ ከሁሉም ይበልጣል ብዬ የማምነው ነገር ግን የእግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ መሆኑን ነው።
7. ንጉስ ሳኦል ዳዊትን ለመግለጽ የተጠቀመው አገልጋዩ የነገረውን "ጀግናና ተዋጊ" ወይም "በአነጋገሩ አስተዋይ የሆነውን" ወይም "እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ የሆነውን" ልጅህን ላክልኝ ሳይሆን ያለው "ከበጎች ጋራ ያለውን ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ" ነው ያለው። ለንጉስነት ተቀብቶ እያለ ለሳኦል አገልጋይ በመሆን መሥራቱ፤ እግዚአብሄር በህይወታችን ሊያደርግ ያሰበውን እንዲፈጽም የእርሱን ጊዜና ሰዓት መጠበቅ እስከዚያ ድረስ ያዘጋጀልንን ሥራ በትጋትና በታማኝነት መፈጸም እንደሚኖርብን ያስተምረኛል።
8. እግዚአብሄር አምላክ ያንን የመሰለ ጥርት ያለና ግልጽ የሆነ ነገር አለመስጠቱ ለሳሙኤል መልካም ሆኖለታል ብዬ የማምነው፤ የዚያን ያህል ግልጽ የሆነ ነገር ቢያገኝ በቀጥታ አባትየውን ገብቶ ዳዊት የሚባለውን ልጅህን አምጣ በማለት ሊጨርሰው ይችል ነበረ፤ ምንም እንኳን እግዚአብሄር የሚጠቀምበት ነብይ ቢሆንም እንደማንኛውም ሰው በእግዚአብሄር እውቀት ማደግ ስለሚኖርበት በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሄር አመለካከት ምን እንደሚመስልና ከሰው እንዴት እንደሚለይ መማር ነበረበት።

# ጥናት አስራ ስድስት 1ኛ ሳሙ 17፡1-58(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ ክፍል የጎልያድን ትጥቅ አንድ በአንድ ሲዘረዝር ወደ ዓዕምሮዬ ያመጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኤፌሶን ምዕራፍ 6 ከቁ11 ጀምሮ ያለው የእግዚአብሄርን እቃ ጦር ሁሉ እንድንለብስ የተነገረን ክፍል ነው። ጎልያድ የተግዳሮት ቃላቱን ሲያሰማ ሳዖልና የእስራኤል ህዝብ ያሳየው ምላሽ በቁ11 ላይ እንደምንመለከተው እጅግ እንደፈሩና እንደደነገጡ ነው።
2. ይህ ሁሉ ሲካሄድ ዳዊት መኖሪያው ሳዖል ቤተ መንግሥት ሆኖ ነገር ግን ከዚያ እየተመላለሰ በጎቹን መጠበቁን ቀጥሎ ቁ15ትን ስናነብ እንመለከታለን። በቁ17-18 ላይ እንደምንመለከተው ዳዊት የተላከው ለወንድሞቹ የሚሆነውን ምግብ ማድረስ ቢሆንም፤ ከዚያ ባሻገር ግን ወንድሞቹ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ደህንነታቸውን ጭምር እንዴት እንዳሉ ተመልሶ ላባቱ ማስታወቅ ነበረ።
3. ዳዊት የተላከበትን ሁለት ነገሮች እንዳከናወነ የምናየው፤ በመጀመሪያ ደረጃ የወሰደውን ስንቅ ለስንቅ ጠባቂው እንዳቀበለ፤ የወንድሞቹን ደህንነት ማወቅ በተመለከተ ደግሞ በዚያው በቁ 22-23 ላይ ጎልያድ ወጥቶ መፎከር የጀመረው ወንድሞቹን አግኝቶ ደህንነታቸውን ይጠይቅ በነበረበት ሰዓት እንደነበረ እናነባለን። ይህንን ድንፋታ ልዩ የሚያደርገው፣ ምንም እንኳን ንጉሱም ሆነ ህዝቡ ባይገነዘቡት፤ ሙሉ ለሙሉ ልቡ በእግዚአብሄር ላይ የሆነውና ለስሙ የሚቀና ሰው በመካከላቸው መገኘቱና ተግዳሮቱን መስማቱ ነው። አሁንም ቢሆን የእስራኤላውያን ምላሻቸው ፍርሃትና ሽሽት እንደሆነ በቁ24 ላይ ይታያል።
4. ለዳዊት ውርደት ሆኖ የታየው ነገር ልክ አምላኩ ማዳን እንደማይችል ህዝብ የህያው እግዚአብሄር ሰራዊት በፍርሃት ተውጦ መሸሹን ነው። ኤልያብ በዳዊት ላይ የተናደደበት ምክንያት በጎቹን በምድረበዳ ጥሎ ወደ ጦርነቱ ቦታ በመምጣቱ ነበረ። ይህንን ጥቅስ፣ በ1ኛ ሳሙ 16፡7 እና በሐዋ ሥራ 13፡22 ከሚገኙት ጋራ በማነጻጸር ስመለከተው፤ እግዚአብሄር በኤልያብ ልብ የረካ እንዳልነበረ፤ ነገር ግን በዳዊት ልብ ደግሞ ደስተኛ እንደነበረ መረዳት ስንችል፤ በተቃራኒው ግን ኤልያብ መልካም ልብ አድርጎ የተቀበለውን እርሱ የልብ አዋቂ ሆኖ ተንኮልና ክፋት የሞላበት ልብ አድርጎ የዳዊትን ልብ ማየቱ አስገርሞኛል።
5. ሳዖል በራሱ የሚለማመደውንና የሚያውቀውን የጦርነት አይነት እንደሚዋጋ አድርጎ ነው ዳዊትን የቆጠረው፤ ስለዚህም ጎልያድንና ዳዊትን በማነጻጸር አሳይቶት በምንም መንገድ ቢሆን ይህንን ሰው ዳዊት ሊያሸንፍ የሚችልበት መንገር እንደሌለ አረጋግጦ ሊነግረው ነው የሞከረው። ዳዊት ደግሞ በህይወቱ የነበረውን ልምምድ ለሳዖል ሲያካፍለውና በእርሱ ዘንድ ውግያ በሰውና በሰው መሃል ሳይሆን በውግያችን ውስጥ እግዚአብሄርን ማስገባትና ድል ማድረግ እንደሚቻል ትምህርት ሲሰጠው እንመለከታለን።
6. ዳዊት የሳዖልን የጦር ልብስና የጦር እቃ እንቢ ለማለት የሰጠው ምክንያት "ያልተለማመድኩት ስለሆነ.." የሚል ነው። ዳዊት በትሩን፣ ድንጋዩንና ወንጭፉን ይዞ ሲወጣ በዚያ አሸንፋለሁ በሚል ትምክህት እንዳልሆነ ከላይ ለሳዖል ሲናገር ካየነው ክፍል መረዳት እንችላለን፤ እርሱ እግዚአብሄር ራሱ ድል እንደሚሰጠው የሚያምን ሰው ነው።
7. ጎልያድ ዳዊትን የናቀው "ደም ግባት ያለው፣ መልከ መልካምና አንድ ፍሬ ልጅ" ስለሆነ አይቶ ናቀው በማለት ቁ42 ይነግረናል። እነዚህ ሁለት ሰዎች የጦር እቃቸው በጣም የተለያየ ሲሆን ዳዊት በቁ45 ውስጥ የሁለቱንም እቃ ጦር በግልጽ አስፍሮት ይገኛል። የጎልያድ፡ ሰይፍ፣ ጦርና፣ ጭሬ ማለትም ሥጋዊ እቃ ጦር ሲሆን፤ ዳዊት የራሱን እቃ ጦር ደግሞ ሲናገር "...ሁሉን በሚችል በእግዚአብሄር ስም እመጣብሃለሁ።" ማለትም የጦር እቃው መንፈሳዊ እንደሆነ ያረጋግጥለታል። መንፈሳዊ የጦር እቃ እንደሚበልጥ ትልቁ ጎልያድ በመዘረሩና የተናቀው ትንሹ ዳዊት በማሸነፉ ግልጽ ሆኖ ይታያል።
8. እስራኤላውያን በቁ24 ላይ ከነበሩበት ታላቅ ፍርሃት ውስጥ ወጥተው በታላቅ ወኔና ፉከራ ጠላታቸውን ለማሳደድ እንዲበቁ ምክንያት የሆነው፤ በሥጋ የሚታየውን ሳይሆን አምላኩን በመተማመን የሚወጣ ደፋር ዳዊት በመሃላቸው በመገኘቱ አሁን ለደረሱበት ድፍረት ለመብቃት አብቅቷቸዋል።

# ጥናት አስራ ሰባት 1ኛ ሳሙ 18፥1-30 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የዮናታን ነፍስ ከዳዊት ነፍስ ጋራ እንደተቆራኘች ይናገራል፤ በዚህም ምክንያት ዮናታን ዳዊትን እንደራሱ አድርጎ እንደወደደውም ስለዚህም ደግሞ ከእርሱ ጋራ ቃል ኪዳንን ለማድረግ እንደወሰነም እናነባለን። ፍቅሩ በተግባር ሲገለጽ የታየኝ በቁ4 ላይ የለበሰውን ካባ ከነጦር ልብሱ፣ ቀስቱን፣ ሰይፉንና መታጠቂያውን ሁሉ አውልቆ ለዳዊት መስጠቱ የፍቅሩን እውነተኛነት ግልጽ አድርጎ ያሳየኛል።
2. ዳዊት በሳዖል ዘንድ ሹመት ለማግኘት ምክንያት የሆነው ነገር፤ ቁ5 እንደሚናገረው፤ ሳዖል በሚልከው ስፍራ ሁሉ ተልዕኮውን በሚገባ ይወጣ ስለነበረ ነው ይለናል። እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ በዳዊት ሹመት ማግኘት ህዝቡ ሁሉ ደስ የተሰኘበት ምክንያት፤ በታላቅ ፍርሃትና ጭንቀት ውስጥ የነበረውን የእስራኤል ህዝብ ገና በወጣትነቱ ያለ መሳሪያ ከጠላቶቻቸው ድልን ካስገኘልን፤ ይህን የመሰለ ስልጣንና የጦር መሳሪያ ከጨበጠማ የሚነካን አይኖርም የሚለው እምነት ይመስለኛል።
3. ሳዖልን ደስ ያላሰኘው ነገር የሴቶቹ መዝፈን ሳይሆን ዘፈኑ ለእርሱ አነስተኛና ለዳዊት ግን የበለጥ ግዳይ የመስጠታቸው ጉዳይ ነው። ሴቶቹ የዚህ ዓይነቱን ዘፈን መዝፈናቸው ትክክለኛ እንደነበረ አምንበታለሁ፤ ምክንያቱም ከዘፈኑት ነገር አንዳቸውም ውሸትነት እንደሌለበት ሳዖል ራሱ እንኳን ሊክደው የማይችለው ነው። ይህ ቀን ወሳኝ ቀን ነበረ ማለት የሚያስችለን ነገር፤ ቁ9 እንደሚነግረን “ከዚያች እለት አንስቶ ሳዖል ዳዊትን በቅንዓት ዓይን ይመለከተው ጀመር።” በማለት በግልጽ ያስቀምጥልናል።
4. ከዳዊት እጅ ዘወትር የማይለይ የምስጋና መሳሪያ ሲኖረው፤ ሳዖል ደግሞ ከአጠገቡ የማይለየውና ለጥፋት ያዘጋጀው ጦር እንደ ነበረው እንመለከታለን። እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ያለን ሰው ከሌሎች ለየት ከሚያደርጉት አንደኛው ነገር፤ በሰዎች ፊት ሞገስ ማግኘት ወይም መፈራት ይኖረዋል (ቁ12)፤ ሁለተኛ ደግሞ የሚያደርገው ሁሉ ይከናወንለታል (ቁ14)
5. እግዚአብሄር ከዳዊት ጋራ መሆኑን ስላወቀ ሳዖል ዳዊትን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየፈራው እንደመጣ ስናይ፤ የእስራኤል ህዝብ ደግሞ በፊታቸው እየወጣ ይመራቸው ስለነበረ ይወዱት ነበረ ይለናል። ሳዖል ቁ17-18 ላይ ስናነብ በአፉ ለዳዊት የሚናገረው ነገር ልጁን ሜሮብን ሊሰጠው እንደሚፈልግ አድርጎ የእግዚአብሄርን ስም ሁሉ በመጠቀም “የእግዚአብሄርንም ጦርነቶች ተዋጋ” በማለት ሲናገረው፤ በልቡ የነበረው ሃሳብ ግን የዳዊት በፍልስጤማውያን መገደል ነበረ።
6. ከዚህ የሳኦል ድርጊት በመመልከት ስለ ባህርይው መናገር የምንችለው ነገር ቢኖር፤ ሳዖል የተናገረውን ነገር ወይም ቃል ኪዳኑን የማይጠብቅ ውሸተኛ ሰው እንደሆነ መናገር እንችላለን። ሳዖል በልጁ ዳዊትን መውደድ የተደሰተው፤ ልጁ እግዚአብሄርን የሚፈራና በእግዚአብሄር የሚተማመን፣ ጀግና ሰው በማግኘቷ፤ ወይም ደግሞ ዳዊት መልካም ትዳር ሊይዝ ነው በሚል ሳይሆን፤ የደስታው ምክንያት የነበረው፤ ዳዊትን በወጥመድ ውስጥ አስገብቶ የሚሞትበትን መንገድ ተመቻቸልኝ ብሎ በማሰቡ ነው።
7. በቁ22 ላይ በሳዖል ላይ የማየው ክፉና እግዚአብሄር የሚጸየፈው ባህርይ ውሸት ነው። “እነሆ ንጉሱ በአንተ ደስ ብሎታል” በማለት ሲናገር ልቡ ዳዊትን በመጥላት እንደተሞላ እያወቀ መዋሸቱ እንኳንስ ለእግዚአብሄር ለህዝቡ ሁሉ ግልጽ ነገር ነው። ሳዖል ደስ የተሰኘው ለዳዊት ማጥፊያ የተመቻቸ ሆኖ ያየው መንገድ ስላገኘ ሲሆን፤ ዳዊት ግን ለሳዖል አማችነት የሚያበቃውን ያላሰበው መንገድ ስለገጠመው ነው።
8. በዳዊት ህይወት ውስጥ የታዩት ስኬቶች፡ ፍልስጤማውያን እንደቀድሞው እስራኤልን ለመውጋት መውጣታቸውን ቢቀጥሉም ድል ግን የዳዊት ነበረ፣ ዳዊት ከሌሎቹ የሳዖል መኳንንት ይልቅ ድልን አገኘ፣ የዳዊት ስሙም እየታወቀ መሄዱ ናቸው። ዳዊት በሄደበት ሁሉ እግዚአብሄር ድልን፣ ሞገስንና በሰው ዘንድ መወደድን ሲሰጠው እንጂ አንድም ጊዜ እነዚህን ነገሮች ለማግኘት ሲሯሯጥ ወይም ሰዎችን ሲለማመጥ አናይም።

## ጥናት አስራ ስምንት 1ኛ ሳሙ 19፡1-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሳዖል በዳዊት ላይ ያደረበት ጥላቻ አድጎ አድጎ ወደ ግድያ ደረጃ እንደደረሰ ነው የምንመለከተው። እግዚአብሄር ግን ይህንን ለንጉስነት የቀባውን ወጣት ብላቴና ለመጠበቅና ለመከላከል ያዘጋጀው መንገድ እንደነበረና ለዚህም መንገድ አድርጎ እየተጠቀመበት ያለው ሰው የንጉሱን የራሱን ልጅ ዮናታንን ነው። ሳዖል ለልጁ ለዮናታ እያስተማረና እያስተላለፈ ያለው ክፉ ነገር፤ መልካምንና ደግን ሰው በክፋት አሸምቆ መግደልን ነው እያስተማረ ያለው።
2. ዳዊት ያደረገው ነገር ለሳዖል መንግሥት ጠቅሟል እንጂ ምንም በደል አላደረገም፣ ፍልስጤማዊውን ሲገድል በገዛ ህይወቱ ቆርጦ ነው፣ ለመላ እስራኤል ታላቅ ድል የመጣው በዳዊት በኩል ነው፣ ሳዖልም ያኔ ዳዊት ባደረገው ነገር ደስተኛ ነበረ፣ ዳዊት ንጹህ ሰው ነው። የዮናታን ዳዊትን ለማዳን ያደረገው ሙከራ ለጊዜው ፍሬአማ ነበረ ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም ዳዊት አይገደልም ብሎ እንዲናገር አደረሰው። ሳዖል የገባውን መሃላ እንዳልጠበቀ እዚያው ወረድ ብሎ በቁ10 ላይ ሊገድለው ሲሞክር እንመለከታለን።
3. በዳዊት ህይወት ውስጥ የምንመለከታቸው ሁለት ዓይነት ጠላቶች፡ አንደኛው ፍልስጤማውያን ማለትም ከውጭ የሚነሱ ጠላቶች ሲሆኑ፤ ሁለተኛው ግን ሳዖል ወይም ከውስጥ የሚነሳ ጠላት እነደሆኑ እናያለን። ዳዊት ውጫዊ ጠላቱን ማለትም ፍልስጤማውያንን ድል ለማድረግ ምንም ችግር አልነበረበትም፤ ሆኖም የውስጡ ጠላት መቼና በምን ሁኔታ እንደሚነሳበት ስለማያውቅ አስቸጋሪ ነበረ። ሁልጊዜም በግል ህይወትም ሆነ በቤተ ክርስትያህ ህልውና ውስጥ፤ ከውስጥ ወይም ከወገኖች የሚመጣውን ጦር ለመቋቋም በጣም አስቸጋሪና አደገኛ እንደሆነ አያጠራጥርም።
4. በዚህ ክፍል ሳዖል ዳዊትን ለመግደል በሚያደርገው ሙከራው ሲጠቀም የምናየው ሰዎችን ወይም አገልጋዮቹን እንደሆነ እንመለከታለን። እግዚአብሄር ደግሞ በተቃራኒው ዳዊትን ለማዳን የሳዖልን የራሱን ልጅ ሚልኮልን ሲጠቀም ነው የምናነበው። ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው፤ ሳዖል በክፋቱ እየባሰና እግዚአብሄርን የበለጠ እያሳዘነ የመጣ እንጂ ለመለወጥና ከሃጥያቱ ለመመለስ ሙከራ እንደማያደርግ ያስረዳናል።
5. በ1ኛ ሳሙ 18፡17 ላይ ዳዊትን መግደልን አስመልክቶ ሳዖል ራሱ እንደማይገለው ነገር ግን ፍልስጤማውያንን እንዲገድሉት እንደሚያደርግ ነበረ የተናገረው፤ 1ኛ ሳሙ 19፡15ትን ስናነብ ግን ሳዖል ራሱ ሊገድለው እንደሚፈልግና ይዘውት እርሱ ጋ እንዲያመጡለት ሲያዛቸው እናያለን። 1) ፍልስጤማውያን እንዲገድሉት ማድረግ 2) ራሱ በጦር ለመግደል 3) አሽከሮቹ እንዲገድሉት በማዘዝና 4) ዳዊት በታመመበት ከነአልጋው ላይ ቀርቦለት ለመግደል።
6. ዳዊት ስዖል ባሳደደው ጊዜ ያደረገው ነገር ቁ18 እንደሚነግረን መሸሽ ነበረ። ታላቁንና እስራኤልን ሁሉ ያንቀጠቀጠውን በባዶ እጁ ገጥሞ ያሸነፈው ዳዊት ያንን ጀግንነቱን በሳዖል ላይ ያልተጠቀመበት ምክንያት እግዚአብሄር በዚያን ጊዜ በንጉስነት የቀባውና ያስቀመጠው ራሱ በፈለገ ጊዜ ያንሳው በማለት ነበረ።
7. ዳዊትን ለመግደል እየተከታተለ ዳዊት ከሳሙኤል ጋራ መሆኑን እያወቀ ምንም ግድ እንዳልሰጠው ስናይ፤ ይህ ሰው የእግዚአብሄርን ነብይ ሳሙኤልንም ቢሆን ምንም የማይፈራ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን። ይህ ሰው የእስራኤል ንጉስ ሆኖ እያለ እነዚህን ለሚያህሉ ረጅም ሰዓታት ራቁቱን ሆኖ መታየቱ ምናልባትም እግዚአብሄር እያደረገ ካለው ነገር እንዲመለስ በውርደት ሊያስተምረው ፈልጎ ይሆን!
8. ሳዖል ሚልኮልን ለዳዊት በሚስትነት የሰጠበት ምክንያት፤ ዳዊትን ለመግደል በሚያደርገው ሙከራ ወጥመድ እንድትሆንበት በማቀድ ነበረ፤ እግዚአብሄር ግን ይህችንው ለወጥመድነት የተዘጋጀች ሴት አዙሮ ለራሱ ዓላማ ማለትም ዳዊትን የሚያድንበት መንገድ አድርጎ ሲጠቀምባት ነው የምንመለከተው። ይህ ለእኛ በአጭሩ የሚያስተምረን ነገር፤ ጠላታችን ለክፉ ያዘጋጀብንን ነገሮች አምላካችን ለእኛ የደህንነት መንገድ አድርጎ እንደሚጠቀምበት እንማራለን።

# ጥናት አስራ ዘጠኝ 1ኛ ሳሙ 20፡1-42(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት ለዮናታን እውነትም ሳዖል ሊገድለው እንደቆረጠ ለማረጋገጥ የተጠቀመበት መንገድ በቁ5-8 የሰፈረው በመባቻ በዓል ላይ ዳዊት ባለመገኘቱና ዮናታን ፈቃድ እንደሰጠው አድርጎ በመንገር ሳዖል ከሚያሳየው ሁኔታ ሃሳቡን መረዳት እንደሚቻል አድርጎ ዳዊት ያቀነባበረው ሃሳብ እነደሆነ እናነባለን። ዳዊት ይህንን ብሎ ሲናገር፤ አሁን ያለበት ሁኔታ እጅግ አደገኛ መሆኑንና በዚሁ ከቀጠለ ሳዖል እንደማይምረውና የሁኔታውን አስከፊነት ለማረጋገጥ የተጠቀመበት አነጋገር ይመስለኛል።
2. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ አምስት ጊዜ ያህል የተጠቀሰው "እግዚአብሄር" የሚለው ቃል ነው። በዚህ ክፍል የሰፈረውን የዮናታንን አነጋገር ስንመለከት፤ የዳዊትና የዮናታን ግንኙነት መሰረት ያደረገው ነገር እግዚአብሄርን እንደነበረ መረዳት በቀላሉ ይቻላል። በቁ13 ላይ ዮናታን ስላባቱ ከተናገረው ነገር ግልጽ ሆኖ የሚታየኝ አንድ እውነት፤ ቀድሞ እግዚአብሄር ከአባቱ ጋራ እንደነበረ፤ ዛሬ ግን እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ እንደሌለ በግልጽ ይጠቁማል።
3. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከተናገራቸው ሃሳቦች እንደምንረዳው፤ ዮናታን ስለዳዊት የወደፊት እጣ ክፍል ማለትም ንጉስ እንደሚሆን በእርግጠኛነት ያወቀ ይመስላል። እግዚአብሄር እንዲፋረዳቸው ዮናታን ሲናገር በተለይም በአሁን ሰዓት እያሳደደው ያለውን አባቱንም እንደሚጨምር አያጠራጥርም።
4. የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማወቅ ዮናታንና ዳዊት የተጠቀሙበት መንገድ፤ በቁ18-23 ላይ ዮናታን ለዳዊት ሲነግረው የምንመለከተውን ሃሳብ በመከተል ነው። እነዚህ ሁለት ሰዎች እንደ ምስክር አድርገው በመካከላቸው ያቆሙት እግዚአብሄርን እንደሆነ ከቁ23 ላይ መረዳት እንችላለን።
5. እኔ እንደሚመስለኝ ሳዖል በዳዊት ላይ የነበረው ጥላቻ እጅግ ከፍተኛ ስለነበረ ምናልባትም የዳዊት ስም በተጠራ ጊዜ ሁሉ ያኔ ጎልያድን በገደለ ሰዓት ሴቶቹ "ሳኦል ሺህ ገደለ፤ ዳዊት አስር ሺህ ገደለ" በማለት የዘመሩርን ወደ አዕምሮው ስለሚያመጣበት ስሙ እንኳን በእርሱ አጠገብ እንዲነሳ የሚፈልግ አይመስለኝም።
6. ዳዊት በግብዣው ላይ ባለመገኘቱና ልጁ ዮናታን ወደዘመዶቹ እንዲሄድ እንደፈቀደለት ሲሰማ በዮናታን ላይ ሳዖል እጅግ እንደተቆጣ በቁ30 ላይ እንመለከታለን። በዚህም ምክንያት የዮናታንን እናት "ጠማማና ዓመጸኛ ሴት" በማለት ሲሳደብ ይሰማል። የዚህ ዓይነቱን አነጋገር እንኳንስ ከአንድ ንጉስ ቀርቶ ከማንኛውም ተራ ሰው የማይጠበቅ ስለሆነ፤ በእኔ አመለካከት መኳንንቶቹ ለእርሱ የነበራቸው አክብሮት እንደሚቀንስባቸው ይመስለኛል።
7. ሳዖልና ዮናታን ሁለቱም በጣም የተቆጡ ቢሆንም፤ ለእኔ የሚታየኝ ልዩነት ሳዖል የሚቆጣው ንጹህ ደም ለምን አላጠፋሁም በሚል ዓይነት ምክንያት ሲሆን፣ ልጁ ዮናታን በሌላ በኩል ደግሞ ሲቆጣ የምናየው፤ ምንም ያላጠፋና ንጹህ ሰው ስለምን ይዋረዳል፣ ስለምንስ ክፉ ይነገርበታል በማለት ስለሌላ ሰው ተቆርቁሮ ነው ሲቆጣ የምናየው። ከዮናታን መለየቱ ዳዊትን እንዳስለቀሰው ብናውቅም እንኳን፤ እኔ እንደሚመስለኝ ዳዊት ከእግዚአብሄር ማደሪያ ከኢየሩሳሌም ወጥቶ በጠላቶቹ ምድር ለመኖር መሰደዱንም ሲያስብ ይመስለኛል ልቅሶውን ያከበደበት።
8. ምንም እንኳን ሳዖል ከራሱ የልብ ክፋት የተነሳ የዳዊትን ህይወት ማጥፋት እንደ ዓላማው አድርጎ የተነሳ ቢሆንም፤ እግዚአብሄር ግን እንደልቤ በማለት በህዝቡ ላይ እንዲነግሥ አስቀድሞ በእርሱ ላይ ዓላም የነበረው ስለሆነ ሳዖል ምንም ያህል የመግደል ጥረት ቢያደርግም እንኳን የእግዚአብሄር ሃሳብ በመጨረሻው እንደተከናወነ እናውቃለን።

## ጥናት ሃያ 1ኛ ሳሙ 21፡1-15(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የካህኑ የአቢሜሌክ የመጀመሪያ ጥያቄው የነበረው “ምነው ብቻህን፣ ሰውስ ለምን አብሮህ የለም?” የሚለው ነበረ። ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ለዳዊት መቅረብ የነበረበት ዋነኛው ምክንያት፤ ዳዊት የንጉስ ሳዖል ሰራዊት መሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው ስለነበረ ሁልጊዜ ወደ ጦርነት ሲላክ ከብዙ ሰራዊት ጋራ ስለሚሆን የዛሬው በብቸኝነት መምጣቱ ለካህኑ ጥያቄ የሚፈጥር ነገር ሆኖ አግኝቶታል። የዳዊት መልስ ምንም ዓይነት የእውነት ቅንጣት የሚታይበት ነገር አይደለም የተናገረው።
2. ይህንን በማለት ዳዊት ለካህኑ አቢሜሌክ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት አንተም ብትሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌላ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ዝርዝር ሁኔታውን ለማወቅ መሞከት አትችልም ለማለት የፈለገ ይመስለኛል። ይህ ከሳዖል ገበታ ይመገብ የነበረው ዳዊት ዛሬ በዚህ ስፍራ የምናየው ማንኛውንም ዓይነት እንጀራ እንዲሰጠው አቢሜሌክን ሲጠይቅ ነው የምንመለከተው።
3. ይህ ዳዊት ሰዎቹ እያለ ለአብያታር በመደጋገም የሚነግረው ነገር በዚህ ስፍራ በትክክል ማየት ባንችልም እንኳን፤ ጌታ የሱስ ስለዚህ ታሪክ በማቴ 2፡25 ላይ ሲናገር በዚህን ጊዜ ሌሎች ከእርሱ ጋራ የነበሩ ሰዎች እንደነበሩ አረጋግጦ ስለሚናገር ዳዊት ታሪክ ለማሳመር የተጠቀመበት ነገር እንዳልሆነ እንረዳለን። ይህ “ሰው ሁሉ የማይበላው” እንጀራ በመባል የተነገረለት እንጀራ በማቴ 2፡26 ላይ እንደምናነበው ከካህናቱ በስተቀር ሌላ ሰው ሊበላው ያልተፈቀደ ቅዱስ እንጀራ እንደነበረ ጌታችን ከተናገረው አነጋገር መረዳት እንችላለን።
4. ምንም እንኳን ኤዶማዊው ዶይቅ በዚህ ክፍል ውስጥ ስንመለከት ምንም እንዳደረገ የተነገረ ባይሆንም፤ ወደኋላ ቆይተን በ1ኛ ሳሙ 22፡9-10 ላይ ስናነብ በዳዊትና በካህኑ አቢሜሌክ መሃል የተካሄደውን ነገር ሁሉ ለሳዖል በመንገርና በ22፡18 ላይ ደግሞ የእግዚአብሄርን ካህናት በሰይፍ የገደለ ሰው እንደነበረ እናነባለን። ዳዊት ምግቡን በእጁ ካስገባ በኋላ በቁ8 ላይ ለውግያ የሚጠቀምበት የጦር መሳሪያ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ነው የምንመለከተው።
5. ዳዊት እንጀራውንና የጦር መሳሪያውን ለማግኘት የተጠቀመባቸው መንገዶች የሚመሳሰሉት፤ ሁለቱንም ጊዜ ዳዊት ምንም ዓይነት እውነት የሌለበት ውሸት በተሞላ መንገድ ነበረ በማታለል እንጀራውንም ሆነ የጦር መሳሪያውን ለማግኘት የቻለው። ሳዖል ለመቀበል የተቸገረው ነገር ግን በጌት የነበሩት ሰዎች ስለዳዊት የተረዱት አንድ እውነት ቁ11 ላይ እንደሚታየው “የምድሪቱ ንጉስ ዳዊት ይህ አይደለምን?” በማለት እግዚአብሄር ለእርሱ ያሰበውን ሃሳብ ሲናገሩ እንመለከታለን።
6. ሳዖል ዳዊትን ባሳደደው ጊዜ ለማምለጥ ሸሽቶ ከእግዚአብሄር ህዝብ መሃል የሄደው የእስራኤል ጠላት ወደሆነውና አንኩስ ወደተባለው ወደ ጌት ንጉስ እንደ ነበረ ከቁ10-11 መረዳት እንችላለን። ይህች የፍልስጤማውያን ከተማ ከዳዊት ህይወት ጋራ የነበራት ግንኙነት፤ ዳዊት የገጠመውና በእግዚአብሄር ሥም ድል ያደረገው ጎልያድ የመጣባት ከተማ እንደሆነች እናውቃለን።
7. ዳዊትን ወደዚህ ሁኔታ ውስጥ ያደረሰው ነገር ፍርሃት እንደነበረ ከቁ12 መረዳት እንችላለን።
8. ዳዊት ከነበረበት ችግር ውስጥ ለመውጣት በተደጋጋሚ ሲጠቀመበት የሚታየው ታክቲክ ውሸትን ነበረ። በእጁ ይዞት የሚገኘው የጎልያድ ሰይፍ ሊያስታውሰው የሚችለውና እየሄደ ከነበረበት የውሸት መንገድ ሊመልሰው ይችል ነበረ የምለው፤ ያኔ ጎልያድን ሲገጥም በባዶ እጅ በእምነት እግዚአብሄርን ተማምኖ ወጥቶ ድል ያገኘው በራሱ እውቀትና ችሎታ እንዳልነበረ፤ ዛሬም ደግሞ ልቡን በእግዚአብሄር ላይ ማሳረፍ እንደሚኖርበት ሊያስታውሰው ይችል ነበረ።

# ጥናት ሃያ አንድ 1ኛ ሳሙ 22፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እግዚአብሄር ዳዊትን የባረከበት ሁለት መንገዶች፤ የመጀመሪያው ናፍቆት እንዳያጠቃው አባትና እናቱን ጨምሮ ቤተሰቡን በሙሉ ሰጠው፤ ሁለተኛው ደግሞ ብቸኝነትና ፍርሃት እንዳያጠቃው አራት መቶ ሰዎችን ሰጠው። እግዚአብሄር ዳዊትን ለመሪነት ያዘጋጀው የተጨነቁ፣ ዕዳ ያለባቸውና የተከፉ ሰዎችን እንዲመራ በመስጠት ነው።
2. ዳዊት እግዚአብሄር በህይወቴ ሊያደርግ ያለውን ነገር አላውቅም ለማለት የፈለገ አይመስለኝም፤ እኔ የሚገባኝ ምንም እንኳን ለእስራኤል ንጉስ እንድሆን የቀባኝ ቢሆን፤ ይህንን ያሰበልኝን ነገር በምን መንገድና፣ መቼ እንደሚያደርገው አላውቅም ማለቱ ይመስለኛል። ዳዊት ከራሱ ሁኔታ አልፎ እያሰበ ያለው ለአባትና ለእናቱ ነው።
3. ዳዊት ከነበረበት ከዐዶላም ዋሻ ወጥቶ ወደ ይሁዳ ምድር እንዲሄድ ነው የተናገረው። ከዓምባው ለቀህ ውጣና ወደ ይሁዳ ሂድ የሚለውን የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ተቀብሎ ወዲያው በመታዘዝ ተነስቶ ወደ ሄሬት ጫካ እንደገባ እንመለከታለን። ዳዊት ላለመታዘዝ ምክንያት ሊሆነው ይችል ነበረ ብዬ የማስበው ነገር፤ ይሁዳ ሳዖል በቀላሉ ሊያገኝና ሊገድለው የሚችልበት ግዛቱ በመሆኑ ራስን ለሞት አሳልፎ እንደመስጠት በመቁጠር ራሱን ማሳመን ይችል ነበረ፤ ሆኖም ዳዊት ከራሱ ጋራ አልተወያየም።
4. ሳዖል ጦሩን አጠገቡ አስቀምጦ መገኘቱ ሁልጊዜ አደጋን የሚያስከትል ነገር እንደሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች ታይቷል፤ ስለዚህም የሳዖል ሹማምንት እንደሚመስለኝ ንግግሩን ከመስማት ይልቅ ልባቸውና ዓይናቸው በጦሩ ላይ ሊሆን እንደሚችል ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ለልጁ ያልተመለሰ ለማንም ይመለሳል ብለው ስለማያምኑ ነው። የካህኑ የአቢሜሌክ ጥፋት ሆነው የተዘረዘሩት ሶስት ነገሮች፤ ለዳዊት እግዚአብሄርን መጠየቅ፣ ስንቅ መስጠትና የጎልያድን ሰይፍ መስጠት ናቸው።
5. ሳዖል ስለዳዊት እየተናገረ የምንሰማው ሁለት እውነት ያልሆኑ ግልጽ ውሸቶች፤ የመጀመሪያው በቁ13 ላይ የምናየው ዳዊት እንዳመጸበት የሚናገረው ሲሆን፤ ሁለተኛውም በዚያው ቁጥር ውስጥ የሚገኝ በእኔ ላይ ያደባል በማለት የሚናገረው ነው። ስለዳዊት ካህኑ የተናገራቸው አምስት እውነቶች፤ 1) የንጉስ አማች ነው 2) የክብር ዘቦች አዛዥ ነው 3) በሳዖል ቤተሰብ መሃል እጅግ የተከበረ ነው 4) ታማኝ ነው 5) ካህኑ ሁሌም ለዳዊት እግዚአብሄርን ይጠይቅለታል።
6. በዚህ ቁጥር ላይ ዳዊት ስለ ዶይቅ ከተናገረው አነጋገር ስለሰውየው ባህርይ መናገር የምችለው አንድ ነገር ቢኖር፤ ወሬ አመላላሽ፣ እምነት የማይጣልበት ወይም ወሬኛ ሰው መሆኑን ነው።
7. የዶይቅ ሁኔታ ወደዚህ ዘመን አምጥቼ ሳገናዝበው፤ ብዙዎች ቤተ ክርስትያን መሄዳቸውን፣ አስራት መስጠታቸውን፣ መዘመር መጸለያቸውን ሳያቆሙ፤ ነገር ግን የጭካኔንና የድፍረትን ሃጥያት በሰዎች ፊት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሄርም ላይ እንኳን ለመፈጸም የማይቀፋቸው፤ የእግዚአብሄርንም አገልጋዮች በጭካኔ እንደሚያሳድዱ ሰዎች ምሳሌ አድርጌ ነው ዶይግን የምመለከተው።
8. በነዚህ ሁለት ሰዎች መሃል የሚታየው ትልቅ ልዩነት ብዬ የማየው ነገር፤ ሳዖል ለሚሆነው ነገር ሁሉና ለተፈጠረው ሁኔታ ሁልጊዜ የሚከሰው ሌላ ሰው እንዳለው ሳይ፤ ዳዊት ደግሞ ለሚያጠፋቸው ማናቸውም ነገሮች ቢሆን በሌላ ሰው ላይ የሚያላክክ ሳይሆን ላጠፋው ነገር ራሱ ሃላፊነትን ለመውሰድ ወደኋላ የማይል እውነተኛ ሰው መሆኑን አያለሁ።

# <u>ጥናት ሃያ ሁለት 1ኛ ሳሙ 23፡1-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ዳዊት ይህንን ወሬ ሲሰማ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ እግዚአብሄርን መጠየቅ ነበረ። እግዚአብሄር ዳዊት እንዲሄድና ቅዒላን ነጻ እንዲያወጣ በተናገረው ጊዜ የህዝቡ ምላሽ የፍርሃትና ለመሄድ ያለመፈለግ ሁኔታ ነበረ። ህዝቡ በፍርሃት እንደተሞሉና ወጥተው ለመዋጋት ፈቃደኞች እንዳልነበሩ በተረዳ ጊዜ ዳዊት ዳግመኛ ወደ እግዚአብሄር መቅረብና መጠየቅ ነው ያደረገው።
2. ዳዊት ለሁለተኛ ጊዜ ከእግዚአብሄር ማረጋገጫን ካገኘ በኋላ ያደረገው ነገር እንደተነገረው ከሰዎቹ ጋራ ወጥቶ ፍልስጤማውያንን መምታትና ያላቸውን ማርኮ መውሰድ ነበረ። ዳዊት ንጉስ ሆኜ ዙፋን እስከምይዝ ድረስ ምንም ነገር አላደርግም ብሎ የሚጠብቅ ሰው ሳይሆን ባገኘው እድል ሁሉ ሊነግሥበት ያለውን ህዝብ የማገልገል እንጂ የመገልገል ልብ ያለው መሪ እንዳልሆነ ያሳያል። የህዝቡ ልብ እስኪዘጋጅ ድረስ የሚያስፈልገውን ያህል ጊዜ በእግዚአብሄር ፊት መቆየት እንጂ እኔ ከተሰማኝ ማንም ቢወድ ባይወድ ግድ የለኝም በሚል ግትር አስተሳሰብ መሄድ መልካም እንዳልሆነ እማራለሁ።
3. አብያታር ወደ ዳዊት በሸሸበት ወቅት ይዞ የሄደው አንድ ነገር ኤፉዱን ነበረ። ሳዖል ዳዊት በእጁ እንደገባ የቆጠረበት ምክንያት፤ ቅዒላ መዝጊያና የብረት መወርወሪያ የነበራት ከተማ ስለነበረች ነው። ዳዊት የተከተለው መንገድ ትክክል እንደሆነና፤ ሳዖል የሄደበት ትክክል እንዳልሆነ ነው እኔ የማምነው፤ ምክንያቱም ዳዊት የእግዚአብሄርን ፈቃድ ሳድርግ አላድርግ ብሎ የሚጠይቅ ሲሆን፤ ሳዖል ግን እያደረገ ያለው ሁኔታውን በመመልከት የራሱ የሆነ ድምዳሜ ላይ በመድረስ እግዚአብሄር በራሱ ፍላጎት ውስጥ ለማስገባት እየሞከረ እንደሆነ ነው ለእኔ የሚታየኝ።
4. የዳዊት ሁለት ጥያቄዎች፡ አንደኛው ሳዖል እኔን ለመውጋት ወደዚህ ይወርዳል ወይ? የሚል ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የቅዒላ ሰዎች አሳልፈው ይሰጡኛል ወይ? የሚል ነበረ። የእግዚአብሄር መልስ ለሁለቱም ጥያቄዎቹ የሰጠው መልስ በአጭሩ "አዎን" የሚል ነበረ። ሰዎች መልካም ነገር አደረግንላቸው ማለት ነገ ተመልሰው እነርሱም ለእኛ መልካም ነገር ያደርጉልናል ብሎ መደምደም እንደማይቻልና፤ ለሰዎች መልካም ነገርን ስናደርግ ከእነርሱ በአንጻሩ መልካም ነገርን በመጠበቅ እንዳይሆን ያሳየናል።
5. ዳዊት በሳዖል እጅ እንዳይወድቅ መጠንቀቅ የነበረበት በየዕለቱ እንደነበረ በቁ14 ላይ እናነባለን። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ዳዊትን የሚጠብቀው እግዚአብሄር ስለማይተኛና እርሱን እረኛው ስላደረገ ሳዖል ያሰበውን ሊያደርግበት በፍጹም እንዳልቻለ ነው የምንመለከተው። እኛም በክርስቶስ ያመንን ሁላችን ጠላታችን ሰይጣን እኛን ለማጥፋት ከመሞከር ወደ ኋላ የሚልበት ጊዜ እንደሌለ፤ ሆኖም እግዚአብሄር በስሙ ከለላ ውስጥ አድርጎ ጠላታችን እንዳያገኘን ጥበቃውን እንደማይለየን እናውቃለን።
6. ዮናታን ወደ ዳዊት መጥቶ በእግዚአብሄር ስም ሲያበረታታው ነው የምንመለከተው፤ የዚህ ዐይነቱ የማበረታቻ መንገድ ለሌሎች ሰዎች ምናልባት ብዙ ላይጠቅምና ላይሰራ ይችላል፤ ሆኖም ዳዊት በህይወቱ የተለማመደውና ተስፋው አድርጎ የያዘው የእግዚአብሄርን ስም ብቻ ስለሆነ ማንም ሊያጽናናው ቢያስፈልግ የአምላኩን ስም በመጥራት እንጂ ሌላ መጽናኛ መንገድ ስለማያውቅ ለእርሱ ትክክለኛ ነገር ነበረ ዮናታን ይዞለት የቀረበው።
7. ዮናታን ወደዳዊት በመምጣቱ የዳዊት ችግር ከእርሱ እንዳልተወገደ እናውቃለን፤ የዮናታን ሃላፊነት ዳዊትን ከነበረበት ችግርና መከራ ውስጥ ነጻ ማውጣት ሳይሆን እጅግ ለሚወደው ለጓደኛው ያለውን ፍቅር የሚገልጽበትና፤ ሁለቱም በእግዚአብሄር ላይ ያላቸው ጠንካራ እምነት ስለነበረ መንፈሱን በማነቃቃት ልቡን ከእግዚአብሄር ዘወር እንዳያደርግ በማበረታታት ተስፋውን ማደስ ነበረ የዮናታን ተልዕኮ።
8. ቁ22 ላይ እንደምናነበው ሳዖል ዳዊትን የሚያየው "እጅግ ተንኮለኛ" ሰው እንደሆነ ነው። ዳዊት ከሳዖል ወጥመድ እያመለጠ ያለው በተንኮሉ ብዛትና በጥበቡ ሳይሆን፤ ሳዖል ያልተረዳው ትልቅ እውነት ይዞ ነው ዳዊት እየተራመደ ያለው፤ ይህም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ ስለሆነ ከተሰወረ ወጥመድ ሁሉ እንዲያመልጥ እንደሚያደርገው ሳዖል አልገባውም።
9. ዳዊት ከሳዖል እጅ ማምለጥ የቻለው ከራሱ ጥበብና ችሎታ የተነሳ እንዳልሆነ ቁ26 ላይ የሆነው ሁኔታ ይነግረናል፤ ሳዖልና ወታደሮቹ ዳዊትንና ሰዎቹን ለመያዝ ተቃርበው በጭንቅ ውስጥ ሳሉ ነው እግዚአብሄር የራሱን መፍትሄ ፍልስጤማውያንን አዘጋጅቶ ነጻ ያወጣቸው።

## ጥናት ሃያ ሶስት 1ኛ ሳሙ 24፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የሰዎቹ ምክር በቁ4 ላይ የምናነበው ይህ ሁኔታ እግዚአብሄር ራሱ ዳዊት ሳዖልን እንዲገድለው አመቻችቶ ያቀረበለት እንደሆነና እርሱም ይህንን የማይገኝ እድል መጠቀም እንዳለበት ነበረ የመከሩት። የሰዎቹ ምክር እግዚአብሄር ለዳዊት በማን በኩል እንደሆነ ባይጻፍልንም ቃል የገባለትን ነገር ተመርኩዘው ነበረ የነገሩት።
2. ከዳዊት ጋራ የነበሩት ሰዎች ጊዜው አሁን ነው የሚል አመለካከት ሲኖራቸው፤ ዳዊት ደግሞ አይ፣ ጊዜው ገና ነው የሚል አመለካከት እንደነበረው ከወሰደው እርምጃና እነርሱም እንዳይወስዱ የከለከለበትን በማየት እንረዳለን። ከዳዊት ጋራ ያሉት ሰዎች ነገሮቹን የሚያዩበት አይን ከሁኔታዎቹ በመነሳት ማለትም ነገሮች መመቻቸታቸውን ከማየት በመነሳት ሲሆን፤ ዳዊት ግን የእግዚአብሄርን ቃል በመመርኮዝ ነው የቃል ኪዳኑን ተፈጻሚነት የሚጠብቀው። "የቀባኋቸውን አትንኩ፤ በነብያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ" መዝ 105፡15
3. በዚህ ክፍል ውስጥ ከአሳዳጁ ሳዖልና ከሚሰደደው ዳዊት ሌላ የማያቸው ብዙዎች ሰዎች እንዳሉበት እመለከታለሁ። በዚህ መሃል ገብተው ለሚፈተፍቱት ሰዎች የነዚህ ሁለት ሰዎች ምላሽ ሙሉ በሙሉ የተለያየ እንደሆነ ነው የሚታየኝ፤ ምክንያቱም ዳዊት አሳዳጁን እንዲገድለው ምክር የተሰጠው ሲሆን እርሱ ግን ምክሩን ውድቅ ሲያደርግ እናያለን፤ በአንጻሩ ግን ሳዖል ከዳዊት አነጋገር እንደምንገነዘበው የመካሪዎቹን ምክር እየሰማ የበለጠ ስህተት ውስጥ እየገባ እንዳለ ነው የሚያስረዳን።
4. ምንም እንኳን ዳዊት የእግዚአብሄርን ፈቃድ ከመፈጸም አንጻር ተነስቶ ያደረገው እንደሆነ ይናገር እንጂ፤ በቁ10 ላይ ደግሞ የራሱን የዳዊትን ልብ አስመልክቶ ስሜቱን ሲናገር "...ራራሁልህ" በማለት ከእግዚአብሄር ቃልም በተጨማሪ ሌላ ምክንያቱን ይነግረናል። ዳዊት ከራሱ እጅ በማውጣት በእግዚአብሄር እጅ አሳልፎ የሚሰጣቸው ሁለት ነገሮች ፍርድና ሕዋ ሥራ 10፡42 እና፣ በቀል ሮሜ 12፡19 ናቸው።
5. እግዚአብሄርን ዳዊት በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚያየው አንደኛው እንደ ዳኛ፣ ሁለተኛው እንደ ጠበቃና፣ ሶስተኛው ደግሞ እንደ ነጻ አውጪ ነው የሚመለከተው።
6. ዳዊት ሳዖል ላደረገበት ክፉ ነገር በዚህ ዓይነት ምላሽ በመስጠት ጠላቱ እንኳን እስኪናገርለት ድረስ መድረሱ ለእኔ የሚያስታውሰኝ ጥቅስ ቢኖር ሮሜ 12፡21 ላይ የተጻፈውን "ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።" የሚለውን ቃል ነው።
7. ሳዖል በዳዊት እጅ ውስጥ እንዲገባ አሳልፎ የሰጠው እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ በቁ18 ላይ ሳዖል ራሱ ሲናገር እንመለከታለን። ስለዳዊት ሳዖል የተናገራቸው ነገሮች፡ ቸርነት እንዳደረገለት፣ ዳዊት በእርግጥ እንደሚነግሥና የእስራኤል መንግሥት በእጁ እንደምትጸና፣ ዘሮቹንና የሳዖልን ስም ከአባቱ ቤት እንዳይደመስስ በመሃላ ይለምነዋል። አንተስ በክፉ የፈለጉህን በመልካም የማሸነፍ ልምድን አዳብረሃል ወይ?
8. ሳዖል ዳዊትን ለመግደል የሰበሰባቸው ሰዎች በሙሉ የተውጣጡት ቁ2 እንደሚነግረን ከእስራኤል እንደሆነ እናነባለን። በ1ኛ ሳሙ 18፤5 ላይ እንደምናነበው ሳዖል ዳዊትን በሰራዊቱ ላይ ሲሾመው ህዝቡ ሁሉና የጦር ሹማምንቱ ሁሉ ደስ እንደተሰኙ እናያለን፤ እነዚህ ይህንን ሁሉ እያወቁ ሳዖልን ለመታዘዝ ብለው ወንድማቸውንና በእግዚአብሄር ፊት በንጽህና ለመመላለስ የሚሞክረውን ሰው ለመግደል መነሳታቸው፤ ለእኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ከራሳቸው ህይወት አልፈው የእግዚአብሄርን ነገር ከማየት አይናቸውን የጨፈኑ ሰዎች ስለሆኑ ይመስለኛል።

## ጥናት ሃያ አራት 1ኛ ሳሙ 25፡1-44 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ናባል ባለጠጋ እንደሆነ፣ ባለጌና ምግባረ ብልሹ እንደሆነ፣ የሚስቱ ስም አቢግያ ይባል እንደነበረ፣ ደግሞም ይህ ሰው ከካሌብ ወገን እንደነበረም ጭምር ተነግሮናል። በባልና በሚስቱ መሃል የምናየውና የተነገረን ግልጽ ልዩነት የባህርይ ልዩነት ነው፤ ይኸውም ሚስት አስተዋይና ውብ ስትሆን፤ አቶ ባል ደግሞ ባለጌና ምግባረ ብልሹ እንደነበረ እናነባለን።
2. ዳዊት ለናባል  ረጅም እድሜንና፣ ሰላም ለራሱና ለእርሱ ለሆነው ሁሉ ነው ሲመኝለት የምናነበው። ዳዊት የናባልን የባህርይ ብልሹነትና ብልግናውን ከተረዳ በኋላ በዚህ ምኞቱ እንዳልቀጠለ ከቁ21 መረዳት እንችላለን፤ ይህንን ክፍል ስንመለከት ዳዊት እንኳን ለእድሜ ርዝመት መመኘት ይቅርና፤ ራሱ ሊቀነጥሰው ተዘጋጅቶ እንደነበረ ይነበባል። ናባል ዳዊት ለእስራኤል ያደረገውን ታላቅ መታደግ ሳይሰማ ቀርቶ አይመስለኝም፤ ነገር ግን ስለባህርይው ከተመለከትነው ለዳዊትና ለሰዎቹ ያለውን ንቀት ለማሳየት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።
3. ቁ3 ላይ የተናገረው የመጽሐፉ ጸሐፊ፣ በቁ17 ላይ የተነገረውን የተናገረው አንደኛው የአቢግያ አገልጋይ እና በቁ25 ላይ ደግሞ ከሁሉ በላይ የምታውቀው ሚስቱ አብግያም በዚሁ አጠራር ትጠራዋለች። እነዚህ ሰዎች እጅግ መልካም እንደነበሩ፣ ምንም እንዳላጠፉ፣ በዙሪያቸው እንደ አጥር ሆነዋቸው እንደነበረና ምንም ክፉ እንዳላረጉባቸው ነበረ ምስክርነቱ። ሁለቱ ጥበብ የተሞሉ እርምጃዎች፡ በቁ18 ላይ የምናየው “ጊዜ አላጠፋችም” የሚለው ሃሳብና፤ በቁ19 መጨረሻ ላይ ደግሞ “ለባሏ ለናባል ግን አልነገረችውም።” የሚሉት ናቸው።
4. እርሱ ዳዊትንና ሰዎቹን የተቀበለው በስድብና በንቀት ሲሆን፣ አቤጌል ግን በአክብሮትና እጅ በመንሳት ነው የተቀበለችው። ናባል በጭራሽ ያልተረዳውና ያልገባው ይህች ሴት ግን የተረዳችው ነገር፤ ዳዊት ዝም ብሎ እንደማንኛውም ሰው እንዳልሆነ፤ ነገር ግን እርሱ የእግዚአብሄርን ጦርነት የሚዋጋና ከፊቱም የንግሥና ዙፋን የሚጠብቀው ሰው እንደሆኖ ገብቷታል።
5. ዳዊት ከሳዖል ጋራ ባሳላፋቸው አስቸጋሪ ጊዜያት በሙሉ በቀልን ይመለከት የነበረው ልክ በሮሜ 12፡19 ላይ “በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራትን እመልሳለሁ” ተብሎ እንደተነገረው ያንን ተከትሎ የሚሄድ ሰው እንደነበረ እንመለከታለን። በዚህ በ1ኛ ሳሙ 25፡26 ላይ ናባልን አስመልክቶ ግን ዳዊት ሁኔታውን ለእግዚአብሄር አሳልፎ መስጠት ሲያዳግተውና በራሱ ሊበቀል ተዘጋጅቶ እንደነበረ፤ ነገር ግን እግዚአብሄር ራሱ ከዚህ ነገር አቢጌልን በመጠቀም እንዳስቆመው እንማራለን።
6. አቢጌል በቁ29 ላይ ሳዖልን አስመልክቶ ብቻ ሳይሆን ማናቸውም የዳዊትን ህይወት ለማጥፋት የሚያሳድድ ሁሉ እንደ ውንጭፍ ድንጋይ እንደሚወረወርና፤ የዳዊት ህይወት መጨረሻ ግን በአምላኩ በእግዚአብሄር ዘንድ በሰላም እንደምትጠበቅ ትናገራለች። ዳዊት ዛሬ ከሚገኝበት ሁኔታው ነገው የተለየ እንደሚሆን ከዚህች ሴት ንግግር የሚጠቁሙኝ፡ እግዚአብሄር ተስፋ እንደሰጠው መናገሯ (ቁ30) ፣ በእስራኤል ላይ በነገሰ ጊዜ (ቁ30) ፣ እግዚአብሄር በጎ ነገር ባደረገልህ ጊዜ እኔን አገልጋይህን አስበኝ (ቁ31) በማለት የተናገረቻቸው አነጋገሮች በግልጽ ዳዊት ዛሬ ባለበት ሁኔታ ነገ እንደማይገኝ ያረጋግጥልናል።
7. የዚህችን ሴት ባህርይ ግልጽ አድርጎ የሚያሳየኝ አንድ ክፍል ብመርጥ ቁ36 ላይ ያለውን “ስለዚህ እስኪነጋ ድረስ ምንም አልነገረችውም” የሚለው ሃሳብ ነው፤ ይህንንም የመረጥኩበት ምክንያት፣ የማታስተውል ሴት ብትሆን በሆነው ነገር በመቆጣት እዚያው ትነግረ እንደነበረና እርሱም በስካር ውስጥ ስለሆነ ደንታ እንደማይሰጠው እናውቃለን፤ ነገር ግን ከስካሩ ወጥቶ መስማት በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ እስከሚሆን ድረስ ታግሳ ለመንገር መወሰኗ አስተዋይነቷን ግልጽ አድርጎ ያመለክታል።
8. እግዚአብሄር ለዳዊት ናባልን ለመበቀል የወሰደበት አሥር ቀናት ሲሆን፤ አሳዳጁን ሳዖልን ለመበቀል ግን ገና በብዙ ምድረበዳዎች ውስጥ ማለፍና ብዙ የመከራ ዘመናትን እንዲያልፍ ተደርጎ በዋሻ፣ በተራራ፣ በሸለቆ ሁሉ ውስጥ ወርዶና ወጥቶ ብዙ ዓመታት፤ ምናልባትም እስከ አስራ አምስት ዓመታት ወስዶ ነው ሳዖልን በመጨረሻው የተበቀለለት፤ በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ማለፉ ለዳዊት ህይወት መሰራትና ለእድገቱ እንደሆነለት አያጠራጥርም።

<u>ጥናት ሃያ አምስት 1ኛ ሳሙ 26፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. እነዚህ የዚፍ ሰዎች በሳዖልና በዳዊት ህይወት ውስጥ እየተጫወቱ ያሉት ሚና የነበረውን ቅራኔ እንዳይበርድና እንዳለ እንዲቆይ የሚያደርጉ ሰዎች ሆነው ነው የማያቸው። ዳዊት ሳዖል እንደተከተለውና ወዳለበት ሥፍራ እንደመጣ ባወቀ ጊዜ ያደረገው ነገር አ ሰላዮችን ልኮ በትክክል የሳዖልን መምጣት ማረጋገጥ ነበረ፤ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ለሁለተኛ ጊዜ ዳዊት ሳዖልን የመግደል ችሎታ እንደነበረውና ነገር ግን ሊገድለው እንደማይፈልግ ሊያረጋግጥለት እንዲችል መንገድ ሲያመቻች ነው።
2. ዳዊት ሊያደርግ ያሰበውን ዓላማ ለማከናወን የወሰዳቸው ሶስት እርምጃዎች፡ የመጀመሪያው በቁ4 ላይ የምናነበው አስቀድሞ ሰላዮችን መላክ ነበረ፤ ሁለተኛው ደግሞ በቁ5 ላይ እንደምናነበው ራሱ ለብቻው ሄዶ ሁኔታዎቹን በትክክል ማረጋገጥ ሲሆን፤ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ከራሱ ጋራ አንድ ሰው ጨምሮ ይዞ በመሄድ ለማድረግ ያሰበውን ነገር ማካሄድ ነበረ። ከዳዊት ህይወት ለመማር እድል የነበራቸው ሰዎች በቁ6 ላይ የምናያቸው አቢሜሌክና አቢሳ ነበሩ።
3. አቢሳ ከዳዊት ጋራ መሄዱ ለዳዊት የህይወት እድገት የሚረዳ ሁኔታ ፈጥሮለታል ብዬ የማስበው፤ አቢሳ ሳዖል እንዲሞት ባቀረበው ሃሳብ ዳዊት ፈተና ለሁለተኛ ጊዜ ተፈትኖ በእግዚአብሄርና በሰው ፊት ቅንነቱን ለማረጋገጥ እድል ሰጥቶታል ብዬ አምናለሁ። አቢሳ ከዳዊት ጋራ አብሮ በመሄዱ ለህይወቱ መመሪያ የሚሆን እድል አግኝቷል የምለው፤ አቢሳ ሳዖልን ለመግደል በጠየቀው ጊዜ ዳዊት ከመለሰለት መልስ ካስተዋለው ግሩም የሆነ ትምህርት እንደሚሆንለት አምናለሁ።
4. ሳዖል በዳዊትም ሆነ በአቢሳ እጅ መገደል እንደሌለበት ዳዊት የሰጠው ምክንያት "እግዚአብሄር በቀባው ላይ እጁን አንስቶ ከበደል ነጻ የሚሆን ማንነው?" የሚለውን የእግዚአብሄር ቃል ከመዝ 105፡15 በመጥቀስ ነበረ። ሳዖል መሞት ካለበት መሞት የሚችልባቸው ብሎ የዘረዘራቸው፡ እግዚአብሄር ራሱ ይቀስፈዋል፣ ቀኑ ደርሶ ይሞታል ወይም ደግሞ በጦርነት ይሞታል የሚሉ ነበሩ።
5. በእኔ አመለካከት ዳዊት በእርሱና በሳዖል ሰራዊት መካከል ሰፋ ያለ ርቀት እንዲኖር የፈለገበት ምክንያት፤ ምንም እንኳን የሳዖል ጦር በእርሱ እጅ ውስጥ እንዳለ ቢያውቅም ሌሎቹ ሶስት ሺህ ሰዎችና የጦር አዛዡ አበኔር ከነትጥቃቸው ስለሆኑ በቀላሉ ተከታትለው ሊይዙና ሊያጠቁ ከሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ ላለመገኘት ይመስለኛል። "እግዚአብሄር የቀባውን ጌታችሁን አልጠበቃችሁምና ሞት ይገባችኋል" በማለት ነው የምናገራቸው።
6. ዳዊት እርሱን የሚያሳድደው ሳዖል ብቻ እንዳልሆነና ሌሎችም በሳዖል ተከልለው ዳዊትን ለማጥፋት የሚያሴሩ እንዳሉ አድርጎ ነው ዳዊት በቁ19 ላይ የሚናገረው። ምንም እንኳን መከራውና ምድረበዳ ለምድረበዳ መንከራተቱ ቢያሰለቸውም፤ በዚህ ክፍል የሚናገረውና ልቡ የሚሰበርበት አንድ ነገር ቢኖር፤ በእግዚአብሄር ርስት ድርሻ እንዳይኖረውና የሚወደውን አምላኩን በኢየሩሳሌም እያመለከ አለመኖሩ ለእርሱ ትልቅ ጉዳት ሆኖበታል።
7. ዳዊት የሳዖል ንስሃ ልባዊ እንዳልሆነ እንዳላመነው የምናየው፤ ከሳዖል ጋራ ንግግራቸውን እንዳበቁ የሚቀጥለው ምዕራፍ 27 ገና ሲጀምር ዳዊት የተናገረውን ነገር ስናይ በሳዖል ንስሃ ላይ ልቡን እንዳላሳረፈ መገንዘብ እንችላለን። ዳዊት ከእግዚአብሄር ምህረት መቀበል ስለሚፈልግ እርሱ ለሳዖል ምህረትን እንዳደረገ ይናገራል፤ እንዲሁም ኢየሱስም ሌላ ሰው ሊያደርግልን የምንወደውን ማንኛውንም ነገር ለሌሎች ሰዎች ያንኑ (ይቅርታ ከሆነ ይቅርታ፣ ምህረት ከሆነ ምህረት) ማድረግ እንደሚኖርብን አድርጎ ነው ያስተማረው።
8. በተለይም ቁ12ትን ስንመለከት እግዚብሄር ዳዊት በሚያልፍበት በዚህ ክፉ መከራ ውስጥ እንኳን እንዳልተለየውና ከጎኑ ሆኖ እርሱ ራሱ ጦርነቱን እየተዋጋለት እንደሆነ የሚያሳየን ሃሳብ እናገኛለን፤ ይኸውም በሳዖልንና በሰራዊቱ ሁሉ ላይ በእንቅልፍን በመጣል ዳዊት ማድረግ ያለበትን እንዲያደርግ ሲያመቻችለት በግልጽ እንመለከታለን።

## ጥናት ሃያ ስድስት ፤ኛ ሳሙ 27፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት በዚህ ቁጥር ላይ ሲያነጋግር የሚገኘው ራሱን በራሱ ነው። ካለበት ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት ዳዊት የወሰነው ነገር፤ ወደ ፍልስጤም ምድር በመሸሽ ከሳዖል እጅ ማምለጥ እንደሚችል ነበረ የወሰነው። ከዳዊት ህይወት እንደምናውቀው፤ አንድን ነገር ለማድረግ ሲያስብና ውሳኔ ማድረግ ሲያስፈልገው በመጀመሪያ ደረጃ በአማካሪነት የሚጠራው እግዚአብሄርን እንደሆነ በተደጋጋሚ በዳዊት ህይወት የታየ ነገር ነው።
2. ወደ ፍልስጤማውያን ብሄድ እኔን ማሳደዱን ይተዋል ብሎ የተናገረው ነገር እውነት ሆኖ እንደተፈጸመ ቁ4ትን ስናነብ እንመለከታለን። ዳዊት ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋራ መከራ እየተቀበለ በእስራኤል እንዳይኖር ነገር ግን የፍልስጤምን ምድር የተሻለ ምርጫ አርጎ እንዲመለከት ያደረገው ነገር የመከራ ርዝመትና የመከራው አላበቃ ማለት ነው።
3. ለዚህ ጥያቄ ምንም እንኳን ትክክለኛ ቁጥር መናገር ባንችል፤ ከዳዊት ጋራ የነበሩት ስድስት መቶ ሰዎች እያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ አራት ወይም አምስት ሰው አለ ብለን ብናስብ በቀላሉ ከሁለት ሺህ አምስት መቶ እስከ ሶስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎችን የህይወት አቅጣጫ የሚቀይር ውሳኔ ነበር የወሰነው። ዳዊት አንኩስን የጠየቀው ለጊዜው ማረፊያ ሥፍራ ሳይሆን "እኖር ዘንድ ሥፍራ ስጠኝ" በማለት ተደላድሎ ለመኖር ነው የጠየቀው።
4. ዳዊትና ሰዎቹ ከፍልስጤም ንጉሥ መኖሪያ ተሰጥቷቸው ሲኖሩ ኑሯቸውን የመሰረቱት በአካባቢው የሚኖሩትን ሰዎች በመዝረፍና ሰዎችን በመግደል ላይ እንደነበረ ከዚህ ክፍል መመልከት እንችላለን። ንጉሱ ለሚጠይቀው ጥያቄ ይመልስ የነበረው በተለያዩ የእስራኤል ከተሞችን ላይ እንደሚዘምት ነበረ፤ ይህ የዳዊት መልስ በጭራሽ እያደረጉ ካሉት ነገር ጋራ የማይገናኝ ነው፤ ምክንያቱም እየዘረፉ ያሉት የእስራኤልን ከተሞች ሳይሆን በቁ8 ላይ የተዘረዘሩትን የተለያዩ የአህዛብ ከተሞችን ነበረ።
5. ዳዊት ያደርገው የነበረውን ነገር ከንጉሱ ለመሰወር ይጠቀምበት የነበረው ሌላ ሃጥያት፤ ማናቸውም ይህንን ድርጊት ሊያጋልጠን ይችላል ብሎ የሚያሰበውን ሴትም ሆነ ወንድ አንድ ሳያስቀር ይገድል እንደነበረም ቁ11 ይነግረናል። ይህ በፍልስጤም የለመደው አንዱን ሃጥያት ለመሸፈን ሲል ሌላ የከፋ ሃጥያት የማድረግ ነገር ዳዊትን በቀጣይ ህይወቱም ውስጥ እንደተከተለውና ከቤርሳቤህ ጋራ የፈጸመውን ዝሙት ለመሸፈን ሲል ባሏ የነበረውን ዖርዮን ማስገደሉን ማስታወስ እንችላለን።
6. ዳዊት ወደ ኋላ መለስ ብሎ ለማሰብ እንኳን የሚሰቀጥጠው አይነት የህይወት ልምምድ ካለፈበት ከዚህ ምዕራፍ ውስጥ መማር የምንችለው ነገር ብዙ የማስበው ነገር ቢኖር፤ ሕይወታችን ሊመሰረት የሚገባውና ዘወትር የህይወቱን ምሳሌነት እየተከተልን ልንኖር የሚገባን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንደሆነ፤ ከሰዎች ህይወት ግን "የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው" እንደሚል ሰዎችን በተመለከተ አኗኗራቸውን እያየንና እየመረጥንና መከተል እንዳለብን እማራለሁ።
7. ዳዊት ሳዖልን ማጥፋት በሚገባውና በእጁ ውስጥ በገባ ጊዜ ሁሉ ይቅርታንና ምህረትን ከመስጠት እንዳልተመለሰ፤ በሉቃስ 6፡31 ላይ "ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትወዱትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው" እንደሚል፤ ዳዊት በ1ኛ ሳሙ 26፡24 ላይ እርሱ ለሳዖል ያሳየውን ምህረት እግዚአብሄር ለእርሱም እንዲያሳየው የለመነ ሲሆን እግዚአብሄርም ልመናውን ሰምቶ እርሱ ምህረት በሚያስፈልገው ሰዓት አትረፍርፎ እንደሰጠው ነው የሚመስለኝ።
8. ዳዊት ለረጅም ጊዜ፤ ምናልባትም ከአሥር አመታት ላላነሰ ጊዜ እግዚአብሂርን እየሰማና በእርሱ ምሪት ሲሄድ ቆይቶ ጊዜው እየረዘመና ችግሩ መፍትሄ አለማግኘቱ ተስፋ ወደመቁረጥና ከእግዚአብሄር ይልቅ አካባቢውንና የራሱን ስሜት ማዳመጥ በመጀመሩ ለመውጣት ወደሚቸገርበት የበለጠ አዘቅት ውስጥ እንዳስገባው እንመለከታለን።

## ጥናት ሃያ ሰባት 1ኛ ሳሙ 28፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳዊት በዚህ ቁጥር ላይ ንጉሱ ያቀረበለት ጥያቄ እስራኤልን ለመውጋት ከእኔ ጋራ ትወጣለህ የሚል ነበረ። ዳዊት ለዚህ ጥያቄ የመለሰው መልስም እኔ ባሪያህ ምን እንደማደርግ አንተ ታያለህ የሚል ነበረ። ለዳዊት ይህ ራሱን ያስገባበት ወጥመድ ቀድሞ ያልተገረዙና የእግዚአብሄርን ሰራዊት የሚገዳደሩ ብሎ ከተናገራቸው ሰዎች ጎን ሆኖ የእግዚአብሄርን ህዝብ ለመውጋት ሊሰለፍ ግዴታ ውስጥ እራሱን አስገብቶ ሲገኝ እንመለከታለን።
2. በቁ3 ላይ ሳዖል በእግዚአብሄር ዓይን ደስ ሊያሰኝ የሚችልና ሲያደርገው የምናገኘው ነገር ከእስራኤል ምድር ላይ ሙታን ሳቢዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን ማጥፋቱ ነው። በራሱ ህይወት ላይ ሲመጣ ሲቸገርበት የምናይው ያባረራቸውን ሙታን ሳቢዎችና መናፍስጥ ጠሪዎች መፈለግ መጀመሩ ሲሆን፤ ይህንንም እንዲያደርግ የገፋው ነገር ፍርሃት የሚባለው ነገር እነደነበረ እናያለን።
3. እንደ እኔ ግምት ከሆነ ሳዖልን ይህንን ያህል እንዲፈራና እንዲጨነቅ ያደረገው ነገር ምናልባትም የራሱን ሰራዊት ቁጥር ፍልስጤማውያን ይዘው ከመጡት የሰራዊት ቁጥር ጋራ በማስተያየት ምንም ሊመጣጠን እንደማይችል በመገመት ሳይሆን አይቀርም ብዬ አምናለሁ። ማንኛውም የእግዚአብሄር ሰው በተጨነቀና መውጫ ባጣ ጊዜ ወደ አምላኩ እንደሚጸልይ ሁሉ፤ ሳዖልም በዚህ ክፍል ውስጥ ሲጨንቀው ወደ እግዚአብሄር መጸለዩ ትክክለኛ ምርጫ እንደመረጠ አምናለሁ።
4. ሳዖል ከእግዚአብሄር መልስ ሲያጣ ቀጥሎ ሊያደርግ የወሰነው ነገር ሙታን ሳቢና መናፍስት ጠሪዎችን መፈለግ ነበረ። ሳዖል ይህንን ከፉ የሆነ ድርጊት ሊያደር ባሰበ ሰዓት ባማከራቸውና፤ ዳዊት ሰራዊቱን ለመቁጠር ባሰበበት ሰዓት በነበረው አማካሪዎች መሃል ለእኔ ግልጽ ሆኖ የሚታየኝ፤ ሳዖል በዙሪያው ያሉት ሰዎች እንኳን እሱን ሊመክሩ ራሳቸውም መናፍስት ጠሪ የሚፈልጉ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ ምክንያቱም ገና ሲጠየቁ ወዲያው አድራሻ ነው የሰጡት፤ ዳዊት ግን እግዚአብሄርን የሚፈሩ ሰዎች ስላሉት በጊዜው ዳዊት ይስማም አይስማ ሊወስድ ያለው እርምጃ እግዚአብሄርን እንደሚያሳዝን የሚነግሩ መልካም መካሪዎች ነበሩት።
5. ሳዖል ሙታን ጠሪዎችንና መናፍስት ሳቢዎችን ከምድሪቱ አጥፍቷል፣ ሌሎች ያልተናገረችው ያደረጋቸው ነገርም አለ፣ እሷም መገደልን እንደፈራች ሌሎችም የገደላቸው ሰዎች እንዳሉም ይጠቁመናል። ሳዖል ከእግዚአብሄር ጋራ ያለው ግንኙነት ከጊዜ ጊዜ እያሽቆለቆለ የሚሄድና ምንም መሰረት የሌለው እንደሆነ አያለህ፤ በተጨማሪም ይህች በአጋንንት መንፈስ የምትኖርና መናፍስትን መጥራት ኑሮዋ ያደረገችን ሴት በእግዚአብሄር ስም መማሉ እርሱ ራሱ እንደዞረበት ያስረዳናል።
6. በእኔ አመለካከት እግዚአብሄር ነው ከሳዖል ራሱን ያራቀው ማለት ያስቸግረኛል፤ ይልቁን የተሻለ አባባል ይሆናል ብዬ የማምነው አነጋገር ቢኖር፤ "ሳዖል ከእግዚአብሄር ርቋል" የሚለው አነጋገር ይመስለኛል። ሳሙኤል በዚህ ቁጥር ላይ የሚያስታውሰው እግዚአብሄር ተናግሮት ሳዖል ግን ለመታዘዝ ፈቃደኛ እንዳልነበረ ሲሆን፤ ይህ ሁኔታ መነሳቱ አስፈላጊ ይሆናል ብዬ የማምነው፤ ሳዖል አለመታዘዙን በንስሃ ያስተካከለበት ጊዜ ስላልነበረ ምናልባት እግዚአብሄር አንድ ሌላ እድል ሲሰጠው ሊሆን ይችላል፤ ሌላው ደግሞ የተገለጠልንን እውነት ሳንታዘዝ ሌላ ተጨማሪ መገለጥ መፈለግ የማይሆን መሆኑን ያስረዳኛል።
7. ሳዖል የሳሙኤልን ንግግር በሰማ ጊዜ በፍርሃት ተውጦ በቁመቱ ሁሉ መሬት ላይ እንደወደቀ ነው ክፍሉ የሚነግረን። ሳዖል ይህንን ሁኔታና ይህንን ጊዜ ለራሱ በሚበጅ ሁኔታ ሊጠቀምበት ይችል ነበረ ብዬ የማምነው እግዚአብሄር ወዲያውኑ ሊቀስፈው ሲችል ቢያንስ የሃያ አራት ሰዓት እድሜ ስለጨመረለት በንስሃ ህይወቱን ከእርሱ ጋራ የማስተካከያ ጊዜ አድርጎ ሊጠቀምበት ይችል እንደነበረ ነው እኔ የሚታየኝ፤ እርሱ ግን ያንን ሁሉ አይቶና ሰምቶ ከወደቀበት በመነሳት በልቶና ጠጥቶ ወደ ቤቱ ነው የሄደው።
8. በቁ7 ላይ ሳዖል ያማከራቸው ሰዎች ማለትም አገልጋዮቹ፤ ዳዊት በእግዚብሄር ፊት ሊበድል ሲል ካናገራቸው ሰዎች የምመለከተው ትልቅና ዋነኛ ልዩነት፤ የሳዖል ሰዎች ሊገባበት ላለው ሃጥያት እንዲያውም መንገዱን ጥርጊያ እንዳደረጉለትና ምናልባትም ራሳቸው እየተለማመዱ ያለውን ነገር አድራሻ እንደሰጡት ስመለከት፤ በዳዊት ጊዜ ግን ሃጥያትን ሊያደርግ እንደተነሳ ኢዮአብ ሲያውቅ ነገሩ እግዚአብሄርን የሚያሳዝንና ባያደርገው እንደሚሻል መከረው፤ ሆኖም ዳዊት ገፍቶ እንደሄደ እናያለን። ኢዮአብ ትክክለኛውን ነገር መጠቆም እንጂ ዳዊትን ካሰበው ሃጥያት መከልከል የእርሱ ሥራ አይደለም።

<u>ጥናት ሃያ ስምንት ፤ኛ ሳሙ 29፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. የፍልስጤም አዛዦች በዚህ ቦታ የጠየቁት ጥያቄ “እነዚህ ዕብራዊያን እዚህ ምን እያደረጉ ነው?” የሚል ነበረ። ይህ ጥያቄ በዳዊትና ከእርሱ ጋራ በነበሩት ሰዎች ቢጠየቅ ይህንን የሚመስል ይመስለኛል፦ “እኛ ዕብራዊያን ሆነን ከእብራዊያን ጎን ለጦርነት መሰለፍ ሲገባን፤ ለመሆኑ ለምንድነው በዚህ ቦታ ከእግዚአብሄር ህዝብ ጠላቶች ጋራ ተሰልፈን ያለነው?” ብለው መጠየቅ ነበረባቸው።
2. በ፤ኛ ሳሙ 27፡10-12 ላይ ዳዊት ከአንኩስ ጋራ በኖረበት ጊዜያት ሁሉ ንጉሱን በማታለልና በመዋሸት ሲመላለስ እንደነበረ ሲነግረን፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስናይ ግን ንጉሱ ዳዊት ያደርገው ይኖረው የነበረውን የህይወት አይነት ሳያውቅ ለዳዊት ከፍተኛ አድናቆት እንዳለው ለሰዎች ሁሉ ሲመሰክርለት ነው የምናየው። በእግዚአብሄር ላይ ታላቅ እምነት የነበረውና በእስራኤል ሁሉ ዘንድ የተከበረው ዳዊት እዚህ ከደረሰ፤ እኛም የእግዚአብሄር ቃል በ፤ኛ ቆሮ 10፡12 ላይ እንደሚነግረን ልንጠነቀቅ ይገባናል።
3. ሳዖል ከዳዊት ተሽሎ ተገኘ የምልበት አንድ ነገር ቢኖር ሳዖል ለጦርነት ራሱን ያሰለፈው ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋራ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ ዳዊት ራሱን ለጦርነት አሰልፎ የምናገኘው ከእግዚአብሄር ህዝብ ጠላቶች ማለትም ከፍልስጤማውያን ሰራዊት ጋራ መሆኑ ነው። እግዚአብሄር ዳዊት በሁለት ክፉ ምርጫዎች ገብቶ እንዳይሰናከል የጠበቀበት መንገድ የፍልስጤምን አለቆች በእርሱ ላይ በማስነሳት ነበረ።
4. በዚህ ውይይት ውስጥ ዳዊትን ወደልቡ ለመመለስ ሊረዳ ይችል ነበረ ብዬ የማስበው አነጋገር፤ በእርሱና በፍልስጤማውያን መሃል ጠላትነት እንጂ ወዳጅነት ሊኖር እንደማይችል ጎልያድን በገደለ ጊዜ የተዘፈነለት ዘፈን ሲነሳ ምናልባትም ወደ ልቡ ሊመልሰው ይችል ነበረ ብዬ አምናለሁ።
5. ዳዊት በዚህ ጦርነት ከፍልስጤም ሰራዊት ጋራ አብሮ ለውግያ መውጣቱ ተመልሶ ፍልስጤማውያንን በመግደል ከሳዖል ጋራ ለመታረቂያ መንገድ አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል ብለው ነው የከሰሱት። የአለቆቹ ፍርሃት ትክክለኛ ሊሆን እንደሚችል ባውቅም፤ እኔ ግን ሳዖል ጉዳዩ የፍልስጤም መሸነፍ ጋራ የተያያዘ ሳይሆን ከራሱ ከዳዊት መሞት ጋራ የተያያዘ በመሆኑ ሳዖል ከዳዊት ጋራ መታረቅ የሚፈልግ ሰው ቢሆን በተለያዩ ጊዜያት የተመቻቸ እድል ዳዊት ራሱ ሰጥቶት አልተጠቀመበትም።
6. ንጉሱ አንኩስ ዳዊት ወደ ጦርነቱ ለመሄድ ላቀረበው ጥያቄ የሰጠው መልስ፤ በእርሱ በኩል ዳዊት እንደ መልዓክ ያለ መልካም ሰው እንደሆነ፤ ነገር ግን የፍልስጤም አዛዦች እንደማያምኑትና ከእነርሱ ጋራ እንዲወጣ እንደማይፈልጉ ነው የነገረው። በእኔ አመለካከት የፍልስጤም ገዦች ያቀረቡት ሃሳብ የተሻለ እንደሚሆን እገምታለሁ፤ ምክንያቱም ዳዊት ላይ ላዩን መልካም ሰው መስሎ በንጉስ ፊት ይታይ እንጂ ከንጉስ በስተኋላ ያደርጋቸው የነበሩ ተንኮሎችን በ፤ኛ ሳሙ 27፡10-12 ተመልክተናል።
7. ዳዊት ንጉሱ በማይኖርበት ሥፍራና ከራሱ ጭፍሮች ጋራ ሲሆን የሚያደርጋቸው ብዙ ክፋቶች እያሉ፤ በንጉስ ፊት ሲሆንና እርሱ ሊያየው በሚችልባቸው ወቅቶችና ሁኔታዎች ላይ ግን ኑሮው በጭራሽ ከሌላ ጊዜው እጅግ የተለየ ስለሆነ እንዲያውም ንጉሱ እንደ መልአክ ነበረ የተቀበለው፤ ስለዚህም ያሞኘውና ያታለለው ንጉሱን እንደሆነ እናያለን።

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ ነኛ ሳሙ 30፡1-31(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዳዊት ወደ መኖሪያቸው ወደ ጺግላግ በተመለሱ ጊዜ የገጠማቸው ነገር፡ ከተማቸው በወራሪ ሃይል ተወሮ ቤቶቻቸው ሁሉና ከተማው ባጠቃላይ ተቃጥሏል፣ የእነርሱ የሆነ ነገር ሁሉ፤ ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው ሁሉ ሳይቀሩ ምርኮኞች ሆነው ተወስደው ነው ያገኙት። እግዚአብሄር በዚህም ውስጥ እንኳን ለዳዊት ቸርነት እንዳደረገለት የምናየው፤ እርሱ ከተሞችን ሲወር ልማዱ ከብትና በጎችን ወስዶ ሰዎችን ሁሉ መግደል ሲሆን፤ እነዚህ ወራሪዎች ግን አንድም ሰው እንዳይገድሉባቸው ተጠብቀላቸዋል።
2. ዳዊትና ሰዎቹ በከተማይቱና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሆነውን ነገር ሁሉ በተመለከቱ ጊዜ ያደረጉት ነገር ማልቀስ እስኪያቅታቸው ድረስ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዳለቀሱ ክፍሉ ይነግረናል። የዳዊት ሰዎች ከከባዱ ለቅሶ በኋላ ያ መፍትሔ ይሆናቸው ይመስል ለመውሰድ የተማከሩት እርምጃ ዳዊትን መግደል ነበረ።
3. ዳዊት በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄርን እንዲፈልግና ወደ እግዚአብሄር እንዲጠጋ ያስገደደው ነገር በእኔ አመለካከት በራሱ ሊወጣው የማይችለው የገባበት መከራ እንደሆነ አምናለሁ። ሳዖልን ሳይሰማ ዳዊትን የሰማበት እኔ የምገምተው ምናልባት ሳዖል እግዚአብሄርን ለመታዘዝ የተዘጋጀ ልብ እንደሌለውና ከዚህ ከመከራው ለመውጣት ብቻ ስለፈለገ፤ ዳዊት ግን ያለበት ሁኔታ ውስጥ ያለው በሁኔታዎች ተገፍቶ እንጂ ልቡ እግዚአብሄርን የሚፈልግ ልብ እንደሆነ ስለሚያውቅ ሳይሆን አይቀርም እላለሁ።
4. ለዚህ ግብጻዊ ሰው ያደረጉለትን የቸርነት እርምጃ እግዚአብሄር ያንንው ተጠቅሞ ነው ጠላቶቻቸውን ለማግኘትን የተወሰደው ምርኳቸው ሁሉ እንዲመለስ ያደረገው። ጠላቶችህን ታገኛቸዋለህ ያልው እግዚአብሄር፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ ያለ አምላክ ስለሆነ፤ ዳዊት በእግዚአብሄር ላይ ያረፈ ሰው ስለሆነ እግዚአብሄርን በመታዘዝ ክስረት እንደሌለ ስለገባው ያመለጠ እንኳን ተመልሶ በእጁ ውስጥ እንደሚያስገባው ስለሚያውቅ ነው ሳይጠራጠር ሰውየውን የረዳው።
5. ዳዊት በቁ13 ላይ የጠየቀው ጥያቄ ያተኮረው በሰውየው በራሱ ላይ ሲሆን፤ በቁ15 ላይ የጠየቀው ጥያቄ ደግሞ ዳዊት ከእርሱ ሊያገኝ በሚፈልገው ነገር ላይ ያተኮረ ነው። ሰውየው ከዳዊት የጠየቃቸው ነገሮች፡- አንደኛው ዳዊት ራሱ እንዳይገድለው ቃል እንዲገባለትና፤ ሁለተኛው ደግሞ ለቀድሞ ጌታው አሳልፎ እንዳይሰጠው ቃል እንዲገባለት ነበረ። ቁ18 እንዲሁም ቁ19 ላይ እንደምናየው ሁለት ቦታ ላይ ዳዊትና ሰዎቹ የተወሰደባቸው ነገር አንድ እንኳን ሳይቀር እንዳስመለሱ እናነባለን።
6. እነዚህ ሰዎች ከነዳዊት ጋራ መሄድ ያልቻሉት እጅግ ደክመው ስለነበረ መሆኑን ቁ21 ግልጽ አድርጎ ይነግረናል። ዳዊት ለደከሙትና ወደኋላ ለቀሩት ሰዎች ሊቀበሉት ሲመጡ ሰላምታ የሰጣቸው ሲሆን፤ እነዚያ ክፉዎችና ምናምንቴ ሰዎች ግን ከተገኘው ምርኮ መካፈል እንደማይችሉና የራሳቸውን ልጆችና ሚስቶች ብቻ መውሰድ እንደሚኖርባቸው ተናገሩ። ዳዊት በቁ23 ላይ የተናገረው የስህተታቸው መነሻ ነው ብዬ አምናለሁ፤ ይኸውም እነዚህ ሰዎች ሁሉንም ነገር በራሳቸው ሃይልና ጥበብ እንዳደረጉት እንጂ እግዚአብሄር ራሱ ከጠላታቸው እንደጠበቃቸውና ምርኳቸውንም ሁሉ በእጃቸው እንደጣለላቸው አለመረዳታቸው ነው።
7. ዳዊት ከዚህ ካሳለፉት ሁኔታ ውስጥ ለእስራኤል ሁሉ ቋሚ ሥርዓት ያደረገው ነገር፤ በጦርነት ጊዜ ወደ ኋላ ቀርቶ ንብረት የሚጠብቅ ሁሉ ሄዶ ጦርነቱን ከተዋጋው እኩል ድርሻ እንዳለውና እኩል እንደሚካፈል ነው የደነገገው። እነዚህ ሰዎች የተንገበገቡለትንና ደክመው ወደኋላ ለቀሩት ወንድሞቻቸው እንኳን ለመስጠት ያልፈለጉትን ምርኮ፤ ዳዊት ምንም ላለፉትና ከእነርሱ ጋራ አብረው ላልነበሩት ወዳጆቹ ለነበሩትና ቀድሞ እነዳዊት በተለያየ ሥፍራ ሲዘዋወሩ ላስተናገዷቸው (ቁ31) ሁሉ ከምርኮው አካፍሎ ሲልክላቸው እናያለን።
8. ዳዊት ከህይወቱ ያጣቸው ነገሮች፡- አለኝ የሚለው ንብረት ሁሉ ተቃጥሎበት ባዶ እጁን ቀርቷል፣ አለኝ የሚላቸው ቤተሰቦቹ፤ ሚስቶቹን አኪናሆምና አቢግያን ጨምሮ ተማርከወበታል፣ በክፉ ጊዜ አብረውት ይቆሙ የነበሩት የቅርብ ጓደኞቹ እንኳን ሊገድሉት እየተማከሩበት ይገኛሉ፣ ማለትም ዳዊት ባዶውን ቀርቷል ማለት እንችላለን።

## ጥናት ሰላሳ 1ኛ ሳሙ 31፥1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. “በዚያን ጊዜ...” ሲል ከላይ በምዕራፍ 30 ውስጥ ዳዊትና ሰዎቹ ያላቸውን ሁሉና ቤተሰባቸውን ሁሉ ባጡበት ሰዓት እግዚአብሄር መልሶ ምርኳቸውንና ቤተሰባቸውን ማስመለስ የቻለበትን ወቅት ሲጠቁመን ነው።
2. እግዚአብሄር ለሳዖል ቸርነት አድርጎለታል የሚያሰኘኝ፤ ሳዖል ወዲያው ተወግቶ ሳይሞት ከእግዚአብሄር ጋራ ያለውን ሁኔታ እንዲያስተካክል ጊዜና እድል ማግኘት ብቻ ሳይሆን የእርሱንም እርዳታ ወይም ፈውስ ለመጠየቅ ወደ እግዚአብሄር ሲመለስ አናይም፤ እርሱ ግን ዘወር ያለው ህይወት ሊሰጠው ወደሚችለው ሳይሆን ሊገድለው ወደሚችለው ወደ ጋሻ ጃግሬው ነበረ።
3. የሳዖል ዋነኛ ፍራቻ የነበረው በአምላኩ ፊት የቀለለና የተዋረደ ሰው ሆኖ መገኘቱ ለእርሱ ምንም ግድ የሰጠው ነገር ሳይሆን፤ ፍልስጤማውያን በእርሱ ላይ ሊያደርጉበት በሚችሉት ነገር በራሱ ህዝብና በጠላቶቹ ፊት ተዋርዶ መገኘቱ ነበረ ከሁሉ ነገር በልጦበት የተገኘው።
4. እግዚአብሄር የተናገረው ሳዖል ለእርሱ ታማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ ምክንያት መንግሥቱን እንደሚያጣ፤ ከዚያም በተጨማሪ ዳዊት ብሎ በጊዜው ስሙን ባይጠራም ለእግዚአብሄር እንደልቡ የሆነ ሰው በእርሱ ቦታ እንደሚነግስ ጭምር የተናገረው በዚህ በሳዖል መሞት ትንቢቱ ጅማሬውን እንዳገኘ እናያለን። ይህንን ያህል ዓመታት ቆጥሮ መፈጸሙ፤ እግዚአብሄር ይናገር እንጂ፤ ከተናገረ ቀኑ አጠረም ረዘመ መፈጸሙ እንደማይቀር ያስተምረናል።
5. የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች የወሰዷቸው እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፤ በመሃላቸው የነበሩት ጀግኖቻቸው ፍልስጤማውያን የሳዖልንና የልጆቹን ሬሳ ወዳኖሩበት ከተማ ሄዱ፤ ሬሳቸውን ከቤትሳን ወደ ኢያቢስ ዘገለዓድ አምጥተው አቃጠሉ፤ አጥንቶቻቸውን ወስደው በኢያቢስ በሚገኘው በአጣጥ ዛፍ ስር ቀበሩ፤ ሰባት ቀን ጦሙ። የኢያቢስ ዘገለዓድ ሰዎችን ሳዖል በነፍሱ ተወራርዶ ከሃፍረትና ከሞት ማዳኑ ዛሬ እነዚህ ሰዎች ለእርሱ ነፍሳቸውን ለመስጠት መወሰን ምክንያት እንደሆነ ነው እኔ የማምነው።
6. ሳዖል እግዚአብሄርን ባለመታዘዙ ምክንያት በደረሰበት ነገር ራሱን ብቻ ሳይሆን የብዙዎች ህይወት የጠፋና የበላሸ ሲሆን፤ ከነዚህም መሃል፡ የእስራኤል ከጠላቱ ፊት ሸሸት(1)፣ ዮናታንና ወንድሞቹ መሞታቸው(2)፣ የሳዖል ጋሻ ጃግሬ መሞት(5)፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ይኖሩ የነበሩት ጭምር መሸሻቸው(7)፣ ፍልስጤማውያን በእስራኤላውያን ከተሞች መኖር መጀመራቸው(7)። አንደኛ ዮናታን ንጉስ ሲሞት ወራሽ ልጅ በመሆኑ ሳሙኤል ባለመኖሩ ምናልባት ህዝቡ ዮናታንን አልፈው ዳዊትን ለማንገስ እንዳይሞክሩ፤ ሁለተኛ ዮናታን ዙፋኑን ባይፈልግም ከሌሎቹ ወንድሞቹ ጋራ ሊከሰት የሚችለውን ሁኔታ እግዚአብሄር ስለሚያውቅ ይሆናል።
7. ከበስተኋላ እነዚህ ሰዎች ያሳለፉትን ሁኔታና ዳዊት በሳዖል ምክንያት ያሳለፋቸውን ነገሮች ሁሉ ለማያውቅ ሰው፤ ይህንን የዳዊት መዝሙር በማንበብ ብቻ ሊናገር የሚችለው ነገር፤ ዳዊት የሳዖል የልብ ጓደኛና እጅግ የሚዋደዱ ሰዎች እንደነበሩ እንጂ፤ በምንም ዓይነት ለዚህን ያህል ዘመን ሊገድለው ለሞከረ ሰው የዘመረው መዝሙር እንደሆነ ለመገመት እንደማይቻል እውቅ ነው።
8. ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ላይ የዘመረውን ፍቅር የተሞላበት ዝማሬ ለመዘመር የቻለው፤ እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ይህ ሰው እግዚአብሄር ይበቀላል፤ የእኔ ሥራ ወይም እግዚአብሄር የሚጠብቅብኝ ሮሜ 13፡8 እንደተነገረው ሁሉ ወንድሜን መውደድ ብቻ ነው ብሎ የሚያምን ስለሆነ፤ ሳዖል ባደረገበት ክፋት ላይ ሳይሆን ሳዖል ለህዝቡና ለሃገራቱ ባደረገው መልካም ነገር ላይ ብቻ ለማተኮር ወስኖ ሌላውን ነገር ለእግዚአብሄር ቅን ፍርድ እንደተወ ነው የማየው።